# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በስኳር ኮርፖሬሽን የወንጂ/ሸዋ ነባር ስኳር ፋብሪካ የማስፋፊያ ሥራ አፈፃፀምና ውጤታማነት ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ/ Executive Summary/ ..... I

ክፍል አንድ ..... 1

መግቢያ ..... 1

የስኳር ኮርፖሬሽን ራዕይ እና ተልዕኮ ..... 2

የስኳር ኮርፖሬሽኑ ዓላማዎች ..... 2

የኮርፖሬሽኑ መብትና ግደታዎች ..... 3

የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ስራዎች ..... 3

የሥራ ተቋራጮች ኃላፊነት ..... 3

በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፍያ ሥራዎች ..... 3

ከአማካሪ መሀንዲሶች የሚጠበቁ ተግባራት ..... 3

የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል ..... 4

የስኳር ኮርፖሬሽን የፋይናንስ ምንጭ ..... 4

የኦዲቱ ዓላማ ፡- ..... 5

የኦዲቱ አካባቢ ..... 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች፡- ..... 5

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት እና የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች፡- ..... 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡- ..... 7

ክፍል ሁለት ..... 8

የኦዲት ግኝቶች ..... 8

የስኳር ፋብሪካ ግንባታ እና ተከላ ዲዛይን ቁጥጥር ..... 8

ክትትል እና ግምገማን በተመለከተ ..... 8

የስኳር ፋብሪካ ግንባታው በታቀደው ጊዜና ..... 11

በተመደበ ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ ..... 11

ለሸንኮራ አገዳ ልማት እርሻ መሬት የመስኖ ጥናት እና ግንባታ ..... 13

በታቀደው ጊዜና በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ ..... 13

የሸንኮራ አገዳ ልማት መሬት ርክክብ፣ የማሽነሪ አቅርቦት እና ..... 15

የመሬት ዝግጅት እና የእርሻ ሥራ/ኦፕሬሽን/ በተመለከተ ..... 15

የሸንኮራ አገዳ ልማት መሬት ርክክብና ዝግጅት ..... 15
የማሽነሪ አቅርቦት ..... 15
የእርሻ ሥራ ኦፕሬሽን ..... 16
ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት ..... 17
አሰጣጥና ሀብትን አዛውሮ መጠቀምን በተመለከተ ..... 17
ዘመናዊ ጥገናና እድሳት እና የማሽነሪና ግብዓት አቅርቦት ..... 18
ለፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀም የሚያበረክተውን አስተዋፆ በተመለከተ ..... 18
ግዥዎች ተጠያቂነት ባለው አግባብ የሚፈፀሙ መሆኑን በተመለከተ ..... 21
ዓመታዊ የንብረት ቆጠራን/Inventory/ን በተመለከተ ..... 23
በመመሪያ መሰረት መወገድ የሚገባቸው ንብረቶችን በተመለከተ ..... 25
የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ ግምገማን በተመለከተ ..... 25
ክፍል ሶስት ..... 27
የመደምደሚያ ሀሳቦች ..... 27
ክፍል አራት ..... 30
የማሻሻያ ሀሳቦች ..... 30

## የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ/ Executive Summary/

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን እና በኢትዮጵያ የክዋኔኦዲት ደረጃዎች መሰረት በስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምና ውጤታማነት ላይ ከ 2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት ዓመት በተከናወኑ ተግባሮች የክዋኔ ኦዲት ያከናወነ ሲሆን የኦዲቱም ዓለማ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ላይ ያካሄዳቸውን የማስፋፍያ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን በተለይ ኦዲቱ በማስፋፍያ ዕቅድ የተያዙ የነባር ማስፋፍያ ሥራዎች፤የፋብሪካ ማስፋፍያ ግንባታ፤ተከላና የኮሚሽኒንግ ሥራዎች፤የመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ ማስፋፍያ ሥራዎችን አፈፃፀም እና ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፕሬሽን አፈፃፀም ውጤታመነትን በመገምገም በአሠራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ከነበሩ በመለየት ችግሮቹ የሚቀረፉበትን ወይም የሚሻሻሉበትን የማሻሻያ ሀሣቦች ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

ኦዲቱ በስኳር ኮርፖሬሽን እና በስሩ ባለ ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የተከናወነ ሲሆን በኦዲቱ የተለዩት ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ተቋራጭ የፋብሪካ ግንባታና ተከላ ሥራውን በገባው የኮንትራት ስምምነት ውል መሰረት አጠናቆ የሙከራ ፍተሻ አድርጎ የማጠናቀቂያ ሰርተፊኬት ሳይሰጠው ፋብሪካው ሙሉ ለሙሉ ሥራ እንዲጀምር መደረጉ፣
- ተቋራጩ ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጂነሪንግ ፓኬጅ አቅርቦትን በውሉ መሰረት የሚያስፈልጉ ንድፎችን/Drawings/ እና ማንዋሎችን ሙሉ ለሙሉ አለማስረከቡ፣
- የመለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ በኮንትራት ውል እ.ኤ.አ መጋቢት 8/2008 ላይ ተቋራጩ ለቀጣሪው ድርጅት በቀን 6,250 ቶን ማምረት የሚችል ፋብሪካ፣ የእንፋሎት ሃይል አመንጪ እስከ መለዋወጫው ዝርዝር ሁኔታው በውል በሰነድ 2/Volume-2/ በተገለፀው መሰረት የሚያቀርብ መሆኑ የተመለከተ ቢሆንም፤ በቃለ-ጉበኤ ቁጥር 049 በቀን እ.ኤ.አ 26/02/2013 የወንጂ/ሸዋ አዲስ ፋብሪካን በተመለከተ በተደረገ የማኔጅመንት ውይይት የፋብሪካ መለዋወጫን አስመልክቶ ተቋራጩ ዝርዝር እስፔስፊኬሽን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑ፤
- የፋብሪካ ግንባታና ተከላ ሥራውን በአማካሪነት የተከታተለው ጄ.ፒ ሙከርጂ/JP MUKHERJI/ የተባለ ካምፓኒ ሲሆን፤የመነሻ ውል እ.ኤ.አ ግንቦት 19/2005 ተፈርሞ የኮንትራት ውሉ ሥራ ላይ የዋለው እ.ኤ.አ ነሀሴ/2005 ሆኖ የመነሻ ውል ማጠናቀቂያ ጊዜ

እ.ኤ.አ የካቲት 2/2008 ቢሆንም ውሉ ለ 8 ጊዜ ተራዝሞ እስከ እ.ኤ.አ መጋቢት 23/2017 እንዲቆይ በመደረጉ ለዘጠኝ ዓመት መዘግየቱ፣እንዲሁም የውል መነሻ ዋጋ እ.ኤ.አ ግንቦት/2005 ዩሮ 558,350/Firm Price/ እና ዩሮ 929,750/Budgeted Price/ ሲሆን 8 ጊዜ የውል ማሻሻያ በመደረጉ ከመነሻ ኮንትራት ዋጋው በድምሩ ዩሮ 4,648,860 ተጨማሪ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ፣

- በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ከ2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን እቅድ አፈፃፀም የፕሮጀክት አገዳ ተከላ/ከአዲሱ ገበሬ ማህበር/ 1,090 ሄክታር ለመትከል ታቅዶ ክንውኑ 277.52/25%/ ሄክታር መሆኑ፣
- በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ከ2007 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በ2,278 ሄክታር የአገዳ ማሳ ላይ የኬሚካል ርጭት በማድረግ የበሽታና ተባይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ግኘው በመዘግየቱ 771.38/34%/ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ተክል ላይ ርጭት መከናወኑ ሲታወቅ፤ የፕሮጀክት የሸንኮራ አገዳ ምርትን 9.5 ቶን/ሄክታር/ወር ለማድረስ ታቅዶ ክንውኑ 5.5/58%/ መሆኑ፣
- በ2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 5,990.35 ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማሳ ላይ ማዳበሪያ መስጠት ታቅዶ አፈፃፀሙ 3,499/58%/ ሆኖ፤ በማሽነሪ ማዳበሪያ 4,065 ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማሳ ላይ ለመስጠት ታቅዶ ክንውኑ 1,683.38 ሄክታር ሲሆን፤በሰው ሃይል ማዳበሪያ መስጠት 6,512.75 ሄክታር ለመሸፈን ታቅዶ አፈፃፀሙ 3,201.88 ሄክታር/49%/ መሆኑ፣
- በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ቅጥር ግቢ ውስጥ አዲስ ወርክ ሾፕ የተጀመረ ሆኖ በአካል ቢታይም፤ ተቋራጩ ሥራውን ያቋረጠ መሆኑ፤

በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ከ2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን ከመስክ ጥገና እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መመልከት እንደተቻለው ለእርሻ ክፍል የሚሆኑ ማሽነሪዎችና ተሸከርካሪዎች፤

- ከባድ ጥገና/Over-haul maintenance/ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ 18 ታቅዶ አፈፃፀሙ በመለዋወጫ እጥረት 9 መሆኑ፣
- ሰርቪስ/Planned maintenance/ በበጀት ዓመቱ በቁጥር 637 ለመሥራት ታቅዶ በመለዋወጫ እጥረት 457 መሆኑ፣
- አነስተኛ ፈረስ ጉልበት ያላቸው የጆንዲር ትራክተሮች መለዋወጫ አለመቅረብ/ሞጆ ደረቅ ወደብ ደርሰው በብር እጥረት ምክንያት መያዝ/፣
- የሸንኮራ አገዳ ወደ ፋብሪካ ማጓጓዣ ጋሪ እጥረት፤ እንዲሁም የአገዳ ጋሪ ጎማ ክምችት በመጋዘን አለመኖር ችግሮች የተስተዋሉ መሆኑ፣
- በመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ አማካሪ ሆኖ የሰራው ድርጅት የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሲሆን የመነሻ ኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ጥር 1/2010 ለ 24 ወራት የሚያገለግል እና እንደ አስፈላጊነቱ የሚታደስ ሆኖ የመነሻ ኮንትራት ዋጋ ብር

17,427,728.99 ውል የፈረመ ቢሆንም፤ የመጀመሪያው የመነሻ ኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ሐምሌ 30/2012 የተጠናቀቀ በመሆኑ እና በመነሻ ኮንትራት ውል በተቀመጠላቸው ጊዜ ሥራዎች ባለመጠናቀቃቸው አራት ጊዜ ውሉ የታደሰ በመሆኑ በድምሩ የአራት ጊዜ ውል መራዘም ብር 30,489,214/174.95%/ ከመነሻ ዋጋ ተጨማሪ ክፍያ መከፈሉ፣

- ኮርፖሬሽኑ የመለዋወጫ ችግርን ለመቅረፍ ድጋፍ የተጠየቀበት የተለያዩ ደብዳቤዎችን መመልከት የተቻለ ቢሆንም ለማሳያ ጳጉሜ 2 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር 07/0/0298/1.1.5 ለወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ አገዳ ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ 26/ሃያ ስድስት/ የቤል ትራክተሮች መለዋወጫ እቃዎች ለክረምት ጥገና ወቅት እንዲያገለግል በአፋጣኝ ከውጭ ሀገር በአውሮፕላን እንዲመጣ የተጠየቀበት እና ነሀሴ 19 ቀን 2007 ዓ.ም ጅቡቲ ወደብ ተከማችተው የሚገኙ የፋብሪካ እቃዎችን በተመለከተ 5 ኮንቴይነር እቃዎች ወደ ሀገር በዋት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር እንዲገቡ ድጋፍ የተጠየቀባቸው መፍትሄ ያላገኙ ደብዳቤዎች ቀርበው ለማየት የተቻለ መሆኑ፣
- ህዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር 29/266/1.1.5 ለስኳር ኮርፖሬሽን በተፃፈ ደብዳቤ ከሞጆ ደረቅ ወደብ ለሚመጡ እቃዎች የገንዘብ ጥያቄን አስመልክቶ ብር 22,019,678.78/ሃያ ሁለት ሚሊዮን አስራ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ስምንት 78/100/ መክፈል ባለመቻሉ የመወረሻ ጊዜያቸው የተቃረቡ 9 እቃዎች ያሉ መሆኑ መታወቁ፣
- የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በ 2007 በጀት ዓመት ወደብ የደረሱ እቃዎችን ወደ ፋብሪካ አጓጉዞ ለመውሰድ ባለመቻሉ ለኮንቴይነር ዲሜሬጅ/በወቅቱ ባለማንሳት የሚከፈል ክፍያ/ እና ለመጋዘን ኪራይ ብር 393,231.33 የከፈለ መሆኑ፣
- የኤክስካቫተር ግዥ መጠይቅ ቁጥር 0745 እና የዶዘር ግዥ መጠይቅ ቁጥር 0653 በአስመጪው ኩባኒያ በኩል እንዲጠገን ክፍያ የተፈፀመ ቢሆንም፤መለዋወጫ ከውጪ ሊያመጡ ባለመቻላቸው ሥራ ላይ ችግር መፍጠሩ፣
- ገደብ ኢንጅነሪንግ ሞዴላቸው 9330፣ 9410 የተባሉ ጆንዲር ትራክተሮችን ለድርጅቱ ካስመጣ በኋላ በ EI-157495 እና PR-803 የተጠየቁ የሰርቪስ እቃዎች/ቺንጋ፣ ሬጉሌተር፣ ቴንሽነር/ የመሳሰሉትን ባለማቅረቡ ሥራ ላይ ችግር መፍጠሩ፣
- በኮርፖሬሽን በኩል ተገዝቶ የቀረበው ቨርሳታይል አርቲኩሌትድ ትራክተር ሰርቪስ ኪት/መገጣጠሚያ እቃዎች/ አብሮ ባለመገዛቱ ሥራ ላይ ችግር የፈጠረ መሆኑ፣
- በቁጥር ሁለት ጆንዲር ትራክተሮች በጊር ቦክስ ብልሽትና ካም ሻፍት ሴንሰር ምልክት አብርቶ የቆሙ ሲሆን በዋስትናው መሰረት እንዲጠገን ህዳር 28/2006 በቁጥር 01/0286/1.1.5 በድርጅቱ በኩል ደብዳቤ ቢፃፍም መልስ ያልተገኘ በመሆኑ ከላይ የተመለከቱት ችግሮች በመሳሪያ ጥገና ክፍሉ የደረሱ መሆናቸው፣

- በወንጂ ስኳር ፋብሪካ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ከውስጥ ኦዲት ሪፖርት መመልከት እንደተቻለው በሲቪል መሀንዲስ ቡድን ስር የሚገኙ በናሙና በታዩ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች እ.ኤ.አ ከጥር 2014 እስከ ታህሳስ 2014 ባሉት ጊዜያት በተቀመጠላቸው በጀትሬት ሊጠቀሙ የሚገባቸው የነዳጅ መጠን 86,683 ሊትር ሆኖ ሳለ የተጠቀሙት የነዳጅ መጠን 138,585 ሊትር ሆኖ 51,902 ሊትር ከበጀት ሬት በላይ ተጠቅመው መገኘታቸው ከሪፖርቱ መረዳት መቻሉ፣
- በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ አጠቃላይ ብዛታቸው 24,785/obsolete Items/ ሆኖ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 43,865,217.16 ሲሆን ያልተወገዱ መሆናቸው፣
- በፋብሪካው የአገዳ አቅርቦት አካባቢ፣ በጥገና ጋራዥ፣ እንዲሁም በአካባቢው በሚገኙ መንገዶች በሚነሳ አቧራ ብናኝ ሰራተኛው በጤና መታወክ ላይ መሆኑን በአካል ለማየት መቻሉ፣

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### የስኳር ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ

1. ዘመናዊ የስኳር ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ በግል የውጭ ባለሀብቶችና በመንግስት ሽርክና በኩባንያ መልክ የተጀመረው በ 1946 ዓ.ም ከአዲስ አበባ 110 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው ወንጂ ከተማ ላይ ሲሆን፤ በወቅቱ በሽርክና ወደ ሥራ የገባው ኤች.ቪ.ኤ የተሰኘ የሆላንድ ኩባንያ ነበር፡፡ ኩባንያው 5 ሺህ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማልሚያ መሬት ተረክቦ ሰኔ 18 ቀን 1943 ዓ.ም ሥራ ጀመረ፡፡ የፋብሪካ ግንባታው መጋቢት 11 ቀን 1946 ዓ.ም ተጠናቆ ስኳር ማምረት ሲጀምር 1 ሺህ 400 ኩንታል ስኳር እያመረተምዕዙን/አንኳር/ እና ባለ አስር ሳንቲም እሽግ ስኳር ለገበያ ያቀርብ ነበር፡፡
2. በወቅቱ የወንጂ አካባቢ በዓለማችን ከፍተኛ ምርት ከሚያስመዘግቡና ለስኳር ምቹ ከሆኑ አካባቢዎች አንዱ ስለነበር ከወንጂ ስኳር ምስረታ ጋር ተያይዞ የወንጂ ከረሜላ ፋብሪካ ሰኔ 1953 ዓ.ም ተቋቁሞ ደስታ ከረሜላ እያመረተ ለገበያ ማቅረብ ጀመረ፡፡ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሥራ ከጀመረ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ በ 1955 ዓ.ም እዛው ወንጂ ላይ የተቋቋመው የሸዋ ስኳር ፋብሪካ በወቅቱ በቀን 1ሺህ 700 ኩንታል ስኳር ያመርት ነበር፡፡
3. ወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በሚል የጋራ መጠሪያ በአንድ አስተዳደራዊ መዋቅር ስር ይተዳደሩ የነበሩት ሁለቱ አንጋፋ ፋብሪካዎች አንድ ላይ በዓመት 750 ሺህ ኩንታል ስኳር ገደማ ያመርቱ ነበር፡፡ የወንጂና ሸዋ ስኳር ፋብሪካዎች ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ካገለገሉ በኋላ በእርጅና ምክንያት እንደቅደም ተከተላቸው በ 2004 ዓ.ም እና በ 2005 ዓ.ም መጨረሻ የተዘጉ ሲሆን፤በምትካቸው አዲስ ዘመናዊ ፋብሪካ ተገንብቶ ከ 2006 ዓ.ም ጀምሮ ስኳር እያመረተ ይገኛል፡፡
4. በ1967 ዓ.ም በተደረገው የመንግስት ለውጥ ምክንያት ስኳር ፋብሪካዎቹ በመንግስት ይዞታ ስር እንዲተዳደሩ ሆኑ፡፡ ይህን ተከትሎ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 58/1970 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን ወንጂ ሸዋና መተሐራ ስኳር ፋብሪካዎችን ጨምሮ አዲስ ከተማና አስመራ ከረሜላ ፋብሪካን እንዲያስተዳድር ተደረገ፡፡
5. የወንጂ ሸዋና የመተሐራ ስኳር ፋብሪካዎችን እንዲሁም የአዲስ ከተማንና የአስመራ ከተማን ከረሜላ ፋብሪካዎች ያስተዳድር የነበረው የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በ 1984 ዓ.ም በሕግ

ሲፈርስ በደንብ ቁጥር 88/85 ወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እራሱን የቻለ የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ እንዲቋቋም ተደረገ፡፡

6. ይህ በእንዲህ እንዳለ ለስኳር ፋብሪካዎች የጋራ አገልግሎት እንዲሰጥ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል አክስዮን ማህበር በሶስቱ ስኳር ፋብሪካዎች፣ በልማት ባንክ እና በመድኅን ድርጅት በአክስዮን መልክ ህዳር 1990 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡

7. በኋላም የድጋፍ ሰጪ ማዕከሉን በማፍረስ የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 504/98 ተቋቁሞ የስኳር ፋብሪካዎችን በመቆጣጠር፣ በፕሮጀክት ልማት፣በምርምር፣በስልጠናና በግብይት ረገድ ድጋፍ ሲሰጥ ቆየ፡፡ ይሁንና ከጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ኤጀንሲው እንዲፈርስ ተደርጎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003 የአሁኑ ስኳር ኮርፖሬሽን ተቋቋመ፡፡ ኮርፖሬሽኑ የስኳር ልማትን በአገራችን በስፋት ለማካሄድ በሚያስችለው መልኩ ተደራጅቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽን ራዕይ እና ተልዕኮ

### ራዕይ

8. በቀጣይ እድገት ላይ በመመስረት በ2016 ዓ.ም በዓለም ተወዳዳሪ ከሆኑ 10 ግንባር ቀደም የስኳር ኢንዱስትሪዎች ተርታ መሰለፍ፣

### ተልዕኮ

9. በአገሪቱ ያለውን እምቅ ሃብት ለማልማት የሚያስችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂና የሰው ሀይል አቅም በማፍራት ስኳር፣የስኳር ተረፈ ምርትና ተጓዳኝ ምርቶችን በማምረት የአገር ውስጥ ፍላጎትን ከማርካት ባሻገር የጎላ የኤክስፖርት ድርሻ በመያዝ የአገሪቱን እኮኖሚ መደገፍ፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽኑ ዓላማዎች

10. በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው

- የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ሌሎች ሰብሎችን ማልማት፣
- ስኳር፣የስኳር ውጤቶችን፣ የስኳር ተረፈ ምርቶችን እና የስኳር ተረፈ ምርት ውጤቶችን በፋብሪካ ማዘጋጀትና ማምረት፣
- ምርቶቹን እና ተረፈ ምርቶቹን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣
- አዳዲስ እና የማስፋፊያ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት፣የዲዛይን ዝግጅት፣የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣የተከላ ኮሚሽኒንግ ሥራዎች እንድካሄዱ ማድረግ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሸንኮራ አገዳና በስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ውጤቶችን በሥራ ላይ ማዋል፣
- አቅሙ ካላቸው የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና ፋብሬኬሽን ሥራዎች በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፣
- በሕግ መሠረት ለሥራው የሚያስፈልገው መሬት ባለይዞታ መሆንና ማልማት፣

- የአገዳ ምርታቸውን ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያቀርቡ አገዳ አብቃዮችን ማበረታታትና መደገፍ፤
- ለስኳር ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፤መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትህምርት ተቋማት ጋር መተባበር፤
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት ናቸው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ መብትና ግደታዎች

11.በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 89/1992 ተቋቁሞ የነበረው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እና በአዋጅ ቁጥር 504/2006 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ መብትና ግደታዎች በደንብ ቁጥር 192/2006 ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

## የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ስራዎች

## የሥራ ተቋራጮች ኃላፊነት

12.ከተቋራጭ የሚጠበቁ ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

1. በገባው ውል መሰረት ዲዛይን መሥራት፣ መፈብረክ በተጨማሪም ለግዥ የሚሆኑ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት፣ንዑስ ኮንትራት/ሰብ ኮንትራክት/ መስጠት፣ፋብሪካ ተከላ ማካሄድ እና ለፋብሪካው እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ ምቹ አቅርቦቶችን በጥንቃቄና በትጋት በውሉ መሰረት አሟልቶ መገኘት፣
2. ተቋራጩ የኮንትራት ውል ሰጪው ድርጅት ያቀረበለትን ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳታዎችን /በመስክም በመገኘት ጭምር/በጨረታው አሸናፊነቱ በተሰጠው በ28 ቀናት ውስጥ በሚገባ መርምሮ ኮንትራት ውል ማፅደቅ አለበት፣
3. ተቋራጩ ለሥራው የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች አሟልቶ ውል ከገባበት ቀን ጀምሮ ወደ ሥራ በመሰማራት ማጠናቀቅ በሚገባው ጊዜና የኮንትራት ዋጋ ማጠናቀቅ ናቸው፡፡

#### በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፍያ ሥራዎች

#### ከአማካሪ መሀንዲሶች የሚጠበቁ ተግባራት

13.ከአማካሪ መሀንዲስ የሚጠበቁ ሶስት **ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል**

1. አማካሪ ድርጅቱ ከተቋራጭ ጋር በሚያደርገው የየቀን ግንኙነት ሥራዎችን በእቅድ በመምራት ትክክለኛው ዲዛይን ሥራ ላይ መዋሉን ክትትል ማድረግ፣
2. ተቋራጭ የፋብሪካ ግንባታና ተከላን በሚገባ ማከናወኑን ግምገማ በማድረግ ማረጋገጥ፣
3. ሥራው በታቀደለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ በእቅድ መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ በየሳምንቱ በመደበኛ ፕሮግራም የፕሮጀክት ግምገማ ማከናወን ናቸው፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል

14.**የስኳር ኮርፖሬሽኑ አደረጃጀት**

ኮርፖሬሽኑ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን በስሩ የሚከተሉትን የሥራ ዘርፎች ይዞ ይገኛል፡፡ እነርሱም፡- የኮርፖሬት ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ኦዲት፣ኮርፖሬት ትራንስፎርሜሽንና ካይዘን ዘርፍ፣ኮርፖሬት መረጃና አይቲ ዘርፍ፣የአገዳ ተክል ልማትና ፋብሪካ ግንባታ ዘርፍ፣ ኦፕሬሽን ዘርፍ፣ኮርፖሬት እቅድና ፕሮጀክት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ፣ ኮርፖሬት የህዝብ ተሳትፎ ዘርፍ፣ ኮርፖሬት ፋይናንስ ዘርፍ፣ኮርፖሬት ሰው ሀብት አመራርና ልማት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ግብይት ዘርፍ፣ምርምርና ስልጠና ዘርፍ እና መስኖ፣ቤቶችና መሰረተ ልማት ዘርፍ ሆነው በስራቸው ከአወቃቀር መግለጫው መረዳት እንደሚቻለው በዳይሬክቶሬቶች የተዋቀረ ነው፡፡

**የስኳር ኮርፖሬሽን የሰው ሃይል/2008 ዓ.ም/**

| ተ.ቁ | የፋብተሪካው /የፕሮጀክቱ/ ስም | በመዋቅርየተፈቀ ደየሰው ኃይል | በስራ ላይ ያለ የሰው ኃይል | ያልተሸፈኔ የስራ መደብ ብዛት | ከመዋቅር በላይ ያለ የሰው ኃይል | ምር መራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተንዳሆ | 9,757 | 3,493 | 6,264 | | |
| 2 | ወንጂ/ሸዋ | 2,605 | 3,726 | | 1,121 | |
| 3 | መተሐራ | 2,514 | 3,203 | | 689 | |
| 4 | ፊንጫአ | 3,205 | 3,270 | | 65 | |
| | አጠቃላይ | 18081 | 13692 | 6264 | 1875 | |

ማስታወሻ፡- በሥራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ቋሚ እና ኮንተራትን ጨምሮ ነው፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽን የፋይናንስ ምንጭ

15.ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር 41,999,731,264(አርባ አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ሳባት መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ አራት ብር) ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ብር 6,042,512,614( ስድስት ቢሊዮን አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ አስራ አራት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፊለዋል፡፡

ከ2006 እስከ 2008 በጀት ዓመታት ያለው የኮርፖሬሽኑ የበጀት አጠቃቀም የፋይናንስ ምንጭ በአባሪ ቁጥር ሁለት ተያይዟል፡፡

**የኮርፖሬሽኑ የአሰራር ስርዓት መግለጫ/System Discription/ በአባሪ ቁጥር ሶስት ተያይዟል፡፡**

**የኦዲቱ ዓላማ :-**

16.የስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ላይ ያካሄዳቸውን የማስፋፍያ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን በተለይ ኦዲቱ በማስፋፍያ ዕቅድ የተያዙ የነባር ማስፋፍያ ሥራዎች፣የፋብሪካ ማስፋፍያ ግንባታ፣ተከላና የኮሚሽኒንግ ስራዎች፣የመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ ማስፋፍያ ሥራዎችን አፈፃፀም እና ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፐሬሽን አፈፃፀም ውጤታመነትን በመገምገም በአሠራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ከነበሩ በመለየት ችግሮቹ የሚቀረፉበትን ወይም የሚሻሻሉበትን የማሻሻያ ሀሣቦች ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

**የኦዲቱ አካባቢ**

17.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ/Potential Audit area/ የስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ባካሄዳቸው የማስፋፍያ ሥራዎች በተለይ በእተርሻና የፋብሪካ ማስፋፍያዎች አፈፃፀም፣ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፐሬሽን አፈፃፀም፣ለማስፋፍያ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አቅርቦት እንዲሁም ከማስፋፍያ ሥራዎች ጋር የተያያዙ የምርምርና ሥልጠና እና የአከባቢ ጥበቃ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለመከናወናቸው እና የማስፋፍያ ሥራዎችም ግልጽነት እና ተጠያቅነትን ባጠናከረ መልኩ የተካሄዱ ስለመሆናቸው ለመገምገም ነው፡፡

**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች:-**

18.ከላይ በተመረጠው የኦዲት አካባቢ /Potential Audit area/ሥር አራት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/ እና አምስት ንዑስ የትኩረት አቅጫዎች /Audit Sub Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የእርሻና የፋብሪካ ማስፋፊያዎች አፈፃፀምን መገምገም
   1.1 የፋብሪካ ግንባታና ተከላ አፈፃፀምን መገምገም
   1.2 የእርሻ ማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምን መገምገም
   1.3 ኮርፖሬሽኑ በሸንኮራ አገዳ ልማት የእርሻ መስፋፋት ምክንያት ለተነሱ/ ለሚነሱ የመሬት ባለይዞታዎች ካሳ ለሚገባቸው የካሳ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን መገምገም
2. የነባር ስኳር ፋብሪካዎች ከማስፋፊያ በኋላ ያለውን የኦፐሬሽን ሥራዎች አፈፃፀምን መገምገም
   2.1 የሸንኮራ አገዳ ልማት የእርሻ ኦፐሬሽን አፈፃፀምን መገምገም
   2.2 የፋብሪካ ኦፐሬሽን አፈፃፀምን መገምገም
3. ለፋብሪካ ማስፋፊያ ግንባታና ተከላ፣ ለመስኖ ግድብና ቦዮች እና የቤቶች ግንባታዎች የተገዙ ዕቃዎች/Materials/ የግዥ አፈፃፀም፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ የስኳር ኮርፖሬሽኑ

ባዘጋጀው የግዥ አፈፃፀም  እና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች መሰረት የተፈፀመ መሆኑን መገምገም

4. በስኳር /ኢታኖልፋብሪካዎች የሚገኙ የምርምርና ስልጠና ጣቢያዎች በምርምር ውጤታቸው የስኳር/ኢታኖል ምርትን ከመጨመር አንፃር ያስገኙትንፋይዳ እና ከፋብሪካዎች ማስፋፋት ሥራ ጋር የአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤ እየተሰራ መሆኑን መገምገም የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት እና የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች፡-

19. እነዚህንም የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ንዑስ የኦዲት የትኩተረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 42 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative Criteria/ የተዘጋጁ ሲሆን፤በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የስኳር ኮርፖሬሽን ኃላፊዎች አስተያት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

- የስኳር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003
- የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የኮንትራት ውል ሰነድ 1 እና 2
- የስኳር ኮርፖሬሽን የአዲስ ሥራ ሂደት ቀረፃ/ቢፒ አር ሰነድ/ የካቲት 2004 ዓ.ም
- የስኳር ኮርፖሬሽን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሀምሌ 2003 ዓ.ም
- የስኳር ኮርፖሬሽን የንብረት አስተዳደር መመሪያ ጥቅምት 2005 ዓ.ም
- ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/1997
- የንብረት ካሳ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣ ደንብ 135/99
- የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች / ከ 2006- 2008 ዓ.ም የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካዎች/
- የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች / ከ 2006- 2008 ዓ.ም የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካዎች/
- አካባቢ ጥበቃን ከሚመለከት አዋጅ
- መልካም ተሞክሮዎችን በማካተት የተዘጋጀ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡-

**የኦዲቱ ወሰን** (Audit Scope)

20. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሻሻለው) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ 2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በስኳር ኮርፖሬሽን የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ የተሰራውን ሥራ ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በስኳር ኮርፖሬሽን ሲሆን፤ በስሩ ባለው በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ነው፡፡

### የኦዲቱ ዘዴ

21. በስኳር ኮርፖሬሽና የስኳር ፋብሪካው ግንባታ እና ተከላው በተከናወነበት ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በመገኘት አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስ፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመገናኘት ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና የማስፋፊያ ሥራዎች አፈጻጸምን አስመልክቶ በአካል በመገኘት መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን የክዋኔ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የስኳር ፋብሪካ ግንባታ እና ተከላ ዲዛይን ቁጥጥር

### ክትትል እና ግምገማን በተመለከተ

22.ለስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ሥራ የፋብሪካ ግንባታ ዝርዝር ዲዛይን፣ የመለዋወጫ አቅርቦት፣ የሲቪል ግንባታ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒንግ/የሙከራ ፍተሻ/ ሥራ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እና የዲይዛን ግምገማ ሊሰራ ይገባል፡፡

23.ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ የፋብሪካ ግንባታ ዝርዝር ዲዛይን፣ የመለዋወጫ አቅርቦት፣ የሲቪል ግንባታ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒንግ ሥራን ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ እና የዲዛይን ግምገማ ሥራ የሰራ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-

### የፋብሪካ ግንባታ ዝርዝር ዲዛይን ክትትልና ግምገማ

24.በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በኮንትራት ውል ሰነድ 1ቢ /Volume- 1B/ እ.ኤ.አ ጥር 21/2008 የጨረታ ሰነድ ስምምነት ሰንጠረዥ ተ.ቁ 9 ላይ ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጅነሪንግ ፓኬጅ ተቋራጩ ጨረታውን እንዳሸነፈ ለቀጣሪው ድርጅት ማስረከብ ያለበት መሆኑን፤ ይህም እንደ ዋና ኢንጅነሪንግ አመልካች ዳታ ሆኖ በኢንፎርሜሽን ሰጪነት ማገናዘቢያ እንደሚያገለግል የተገለፀ ቢሆንም፤ተቋራጩ በውሉ መሰረት የሚያስፈልጉ የፋብሪካው ንድፎችን/Drawing/ እና ማንዋሎችን ሙሉ ለሙሉ ያላስረከበ መሆኑ ታውቋል፡፡

25. ስለሁኔታው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ኦፕሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ

ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጂነሪንግ ፓኬጅ አቅርቦትን በተመለከተ ተቋራጩ በውሉ መሰረት የሚያስፈልጉ ንድፎችን/Drawings/ እና ማንዋሎችን ሙሉ ለሙሉ አለማስረከቡን ገልፀዋል፡፡

26. ኮርፖሬሽኑ ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጂነሪንግ ፓኬጅ አቅርቦትን፣ ማንዋሎችን ከተቋራጩ በውሉ መሰረት መረከብ አለመቻሉ የፋብሪካው ግንባታና ተከላ ሥራው በታቀደው ዲዛይን መሰረት መሰራቱን ለመገምገም የማያስችለው ሲሆን፤ ለወደፊቱም በፋብሪካው የሥራ ሂደት ዘመን ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስቸግር ይሆናል፡፡

## የመለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ

27.የመለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ እ.ኤ.አ መጋቢት 8/2008 በድርጅቱ እና በተቋራጩ በተፈረመው የኮንትራት ውል ላይ ተቋራጩ ለቀጣሪው ድርጅት በቀን 6,250 ቶን ማምረት የሚችል ፋብሪካ፣ የእንፋሎት ሃይል አመንጪ እስከ መለዋወጫው ዝርዝር ሁኔታው በውል በሰነድ 2/Volume-2/ በተገለፀው መሰረት የሚያቀርብ መሆኑ የተመለከተ ቢሆንም፤ በቃለ-ጉበኤ ቁጥር 049 በቀን እ.ኤ.አ 26/02/2013 የወንጂ/ሸዋ አዲስ ፋብሪካን በተመለከተ በተደረገ የማኔጅመንት ውይይት የፋብሪካ መለዋወጫን አስመልክቶ ተቋራጩ ዝርዝር እስፔስፊኬሽን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑን በማሳወቁ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ አቅራቢነት የመለዋወጫ አቅርቦት ለማግኘት መነጋገርና በቀጣይ የሚስተካከልበትን መንገድ መፈለግ የሚል ውሳኔ የተቋራጩን ፍቃደኛ አለመሆን እና የድርድር ሀሳብ የሚገልፅ ቃለ-ጉባኤ መመልከት ተችሏል፡፡

28. እንዲሁም የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ሥራውን በ 2005 በጀት ዓመት የምርት ዘመን የጀመረ አዲስ ፋብሪካ ሆኖ እያለ በ 2007 በጀት ዓመት ተቋራጩ ዋናውን ተፈላጊ የወፍጮ ማስነሻ መለዋወጫ /ኤም ሲሲ ጊር ቦክስ/ ባለማቅረቡ ምክንያት የአሮጌው ፋብሪካ አነስተኛ ጉልበት ያለውን ወፍጮ ማስነሻ ከፍተኛ ጉልበት ያለውን አዲሱን ፋብሪካ ለማስነሳት ሥራ ላይ በመዋሉ በዚህ ሳቢያ 112 ሰዓት የሥራ ጊዜ የባከነ መሆኑ ታውቋል፡፡

29.ስለሁኔታው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ኦፕሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ

30.ተቋራጩ የፋብሪካ ኦፐሬሽን ሥራ መለዋወጫን አስመልክቶ ዝርዝር እስፔስፊኬሽን ለመስጠት ፍቃደኛ ስላልሆነበት ምክንት ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ያልሰጡ ሲሆን፤ ከአሮጌዎቹ ፋብሪካዎች መለዋወጫ ያስፈለገበት ምክንያትን በተመለከተ በሰጡት መልስ የስኳር ፋብሪካ ማሽነሪዎች ድንገት ሊበላሹ የሚችሉና ብልሽታቸውም ከፍተኛ የምርት ማስተጓጎል ጊዜያት የሚያስከትሉ መሆኑን ገልፀው፤ በዋናነት ማንኛውም ፋብሪካ ተተክሎ ወደ ሥራ በሚገባ ጊዜ የውል ስምምነቱ የሚፈቅድ በመሆኑ ተቋራጩ የሁለት ዓመት መለዋወጫ ማቅረብ ያለበት ቢሆንም፤ ፋብሪካውን ሙሉ ለሙሉ ባለማጠናቀቁና ኮሚሽኒንግ/የሙከራ ፍተሻ/ ባለማድረጉ የመለዋወጫ አቅርቦቱን ተግባራዊ ማድረግ ያልቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

31.ኮርፖሬሽኑ የመለዋወጫ እስፔስፊኬሽን ከተቋራጩ በውሉ መሰረት መረከብ አለመቻሉ የፋብሪካው ግንባታና ተከላ ሥራው በታቀደው ጊዜ እንዲጠናቀቅ የማያስችለው ሲሆን፤ ለወደፊቱም ፋብሪካውን ለሚያጋጥሙ የመለዋወጫ ችግሮች ትክክለኛውን የመለዋወጫ እስፔስፊኬሽን ለይቶ በግዥ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስቸግር ይሆናል፡፡

## የሲቪል ግንባታ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒንግ

32.እ.ኤ.አ ጥር 21/2008 በቀጣሪው ድርጅት እና በተቋራጩ በተፈረመው ኮንትራት ውል እስፔሻል ኮንዲሽን/ልዩ ሁኔታ/ በንዑስ ቁጥር ጂሲሲ/GCC 27.6.1/ ላይ በተመለከተው መሰረት የፋብሪካው የሥራ ዋስትና ፍተሻ/Guarante Test/ ሶስት ጊዜ በሚከናወንበት ወቅት ማንኛውም የፋብሪካው አካል /Equipment/ ውጤታማ ካልሆነ ጥገና ሳያስፈልገው በተቋራጩ ዋስትና አዲስ ተተክቶ የዋስትና ማረጋገጫውም ለአንድ ዓመት እንደሚራዘም የተመለከተ ቢሆንም፤የወንጂ/ሸዋ አዲሱ የማስፋፊያ ፋብሪካ ሥራውን እንዲጀምር የተደረገው ተቋራጩ የሥራ ብቃት ፍተሻ/ Commissioning/ ሳያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

33. ኮርፖሬሽኑ ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጂነሪንግ ፓኬጅ አቅርቦትን፣ ማንዋሎችን እና የመለዋወጫ እስፔስፊኬሽን ከተቋራጩ በውሉ መሰረት መረከብ አለመቻሉ የፋብሪካው ግንባታና ተከላ ሥራው በታቀደው ዲዛይን መሰረት መሰራቱን ለመገምገም የማያስችለው ሲሆን፤ ለወደፊቱም በፋብሪካው የሥራ ሂደት ዘመን ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስቸግር ሲሆን፤ የፋብሪካውን መላ አካላት የሙከራ ፍተሻ አስደርጎ አለመረከብም የተጓደሉ እና ለምርት ሂደቱ አስፈላጊ የሆኑ መለዋወጫዎችን በራስ አቅም ለመተካት አላስፈላጊ ወጪ እንዲያወጣ ያደርገዋል፡፡

34. በተጨማሪም ተቋራጩ የፋብሪካ ግንባታና ተከላ ሥራውን በገባው የኮንትራት ስምምነት ውል መሰረት አጠናቆ የሙከራ ፍተሻ አድርጎ የማጠናቀቂያ ሰርተፊኬት ሳይሰጠው ፋብሪካው ሙሉ ለሙሉ ሥራ እንዲጀምር ተደርጓል፡፡ ሆኖም ፋብሪካው የብቃት ፍተሻ ሳይደረግለት ሥራ እንዲጀምር የተደረገበትን ምክንያት የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

35. ስለሁኔታው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ኦፕሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ አዲሱ የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ሥራውን ያለ ምንም ኮሚሽኒንግ/የሙከራ ፍተሻ/ የጀመረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

36. ኮርፖሬሽኑ የፋብሪካውን መላ አካላት የሙከራ ፍተሻ አስደርጎ አለመረከቡ የተጓደሉ እና ለምርት ሂደቱ አስፈላጊ የሆኑ መለዋወጫዎችን በራስ አቅም እንዲተካ በማድረግ አላስፈላጊ ወጪ እንዲያወጣ ያደርገዋል፡፡

## የስኳር ፋብሪካ ግንባታው በታቀደው ጊዜና

## በተመደበ ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ

37.የክትትልና የቁጥጥር አሰራር ስርዓትን በመዘርጋት እና ተግባራዊ በማድረግ የፋብሪካ ግንባታ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ እስከ ኮሚሽኒንግ ሥራ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

38.ኮርፖሬሽኑ የክትትልና ቁጥጥር አሰራር ስርዓትን ዘርግቶ የፋብሪካ ግንባታ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ እስከ ኮሚሽኒንግ ሥራ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ያስደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ የመነሻ ውል ስምምነት በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እና በዩታም ሱክሮ ቴክ/UTTAM Sucro Tech/ መካከል እ.ኤ.አ መጋቢት 8/2008 ሲሆን፤ የኮንትራት ውል መነሻ ዋጋ ዩኤስ ዲ/USD/ 91,676,300 እና ብር 113,214.30 መሆኑ ሲታወቅ፣ ፋብሪካው መቼ እንደሚጠናቀቅ ከውል መነሻው ዋጋው ጋር አብሮ ያልተገለፀ ሲሆን፣ሥራው በፓኬጅ ደረጃ ተከፋፍሎ ለተቋራጮች የተሰጠ በመሆኑ ለሃይል ማመንጫ ፕላንት/Power Generation plant/ እስከ ኮሚሽኒንግ ከ 96 እስከ 104ሳምንት/ከአንድ ዓመት ከአስራድ ወር እስከ ሁለት ዓመት/ የሚወስድ መሆኑ በውል ሰነዱ ላይ የተገለፀ ሲሆን፤ የእንፋሎት ሃይል ማመንጫ ፕላንት/Steam Generation Plant/ እስከ ኮሚሽኒንግ ከ 100 እስከ 108 ሳምንት/ከሁለት ዓመት እስከ ሁለት እስከ ሁለት ዓመት ከአንድ ወር/ የሚያስፈልግ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን፤ የፋብሪካውን ሥራ በተቋራጭነት ለሰራው ለዩታም/ UTTAM/ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተገኘ መረጃ ተቋራጩ፡ የመነሻ ውል ጊዜው እ.ኤ.አ ከመጋቢት 8/2008 እስከ እ.ኤ.አ ሐምሌ 11/2009 መሆኑ ተመልክቶ በወቅቱ ባለመጠናቀቁ የመጀመሪያው የጊዜ ማሻሻያ እ.ኤ.አ ከህዳር 4/2009 እስከ እ.ኤ.አ የካቲት/2011፤ ሁለተኛ የጊዜ ማሻሻያ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 5/2012 የተደረገ ሆኖ ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ ግንቦት 2013 በአማካሪው በተገለፀው መሰረት ከጥቃቅን ሥራዎች በስተቀር ተጠናቆ ፋብሪካው መደበኛ ሥራውን እንዲጀምር ቅድሚያ በመሰጠቱ የቀሩትን ሥራዎች ወደ ፍፃሜ ማድረስ ያልተቻለ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ፕሮጀክቱ መጠናቀቅ ከሚገባው ከእ.ኤ.አ ሐምሌ 11/2009 እስከ ፕሮጀክቱ የተጠናቀቀበት እ.ኤ.አ ግንቦት 2013 ድረስ/ጥቃቅን ሥራዎች መኖራቸውን ታሳቢ በማድረግ/ አራት ዓመት የጊዜ መራዘም የሚያመለክት መሆኑ ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡ የተመደበ በጀትን በተመለከተ ውሉ ላይ የተመለከተው መነሻ ዋጋ የማይንቀሳቀስ/Fixed/ በመሆኑ ጭማሪ ያልታየበት መሆኑ ታውቋል፡፡

39. በተጨማሪም የፋብሪካ ግንባታና ተከላ ሥራውን በአማካሪነት የተከታተለው ጄ.ፒ ሙከርጂ/JP MUKHERJI / የተባለ ካምፓኒ ሲሆን፤የመነሻ ውል እ.ኤ.አ ግንቦት 19/2005 ተፈርሞ

የኮንትራት ውሉ ሥራ ላይ የዋለው እ.ኤ.አ ነሀሴ/2005 ሆኖ የመነሻ ውል ማጠናቀቂያ ጊዜ እ.ኤ.አ የካቲት 2/2008 ቢሆንም ውሉ ለ 8 ጊዜ ተራዝሞ እስከ እ.ኤ.አ መጋቢት 23/2017 እንዲቆይ በመደረጉ ለዘጠኝ ዓመት መዘግየቱ ታውቋል፡፡

40. እንዲሁም የውል መነሻ ዋጋ እ.ኤ.አ ግንቦት/2005 ዩሮ 558,350/Firm Price/ እና ዩሮ 929,750/Budgeted Price/ ሲሆን 8 ጊዜ የውል ማሻሻያ በመደረጉ የሚከተሉት ተጨማሪ የዋጋ ስምምነት ተደርገዋል፡፡
    - 1ኛ ማሻሻያ ውል እ.ኤ.አ ሐምሌ 18/2010 ተጨማሪ ዋጋ ዩሮ 105,250
    - 2ኛ ማሻሻያ ውል እ.ኤ.አ እስከ መጋቢት 23/2012 የማሻሻያ ዋጋ ዩሮ 1,011,875
    - 3ኛና 4ኛ ማሻሻያ ውል የዋጋ ጭማሪ ያልተደረገባቸው ሲሆን፤
    - ከ 5ኛ እስከ 8ኛ ፋብሪካው የሙከራ ፍተሻ ያልተደረገለት በመሆኑ የጊዜ ቆይታዎች ብቻ ሲሆኑ፣
    - ሆኖም በ 8ኛው የማሻሻያ ወቅት እ.ኤ.አ እስከ መጋቢት 23/2017 የሚቆይ ሲሆን፤የማሻሻያ ዋጋ ውሉም ዩሮ 3,531,735 መሆኑ የተዋቀ ሲሆን ከመነሻ ኮንትራት ዋጋው በድምሩ ዩሮ 4,648,860 ተጨማሪ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

41. ስለሁኔታው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ኦፕሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ የፋብሪካውን ግንባታ በጨረታ ሂደት አሸንፎ ማን እንደወሰደ በምንስ ያህል መነሻ የኮንትራት ዋጋ ተዋዋለ መቼስ ጀምሮ መቼ ለማጠናቀቅ ተዋዋለ ከመነሻ ውሉ ባሻገርም የጊዜ መሻሻል ውል የተፈፀመ ከሆነ እንዲያብራሩ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ለመነሻ ኮንትራት ዋጋና ሥራ ለመጀመር ውል የተፈፀመበትን ጊዜ ብቻ በመገለፅ፣ለኮንትራት ማጠናቀቂያ ጊዜ እና ለተራዘመ ጊዜ ጥያቄዎች መልስ ያልሰጡ ሲሆን፤

42. እንዲሁም በድርጅቱና በአማካሪው መሀንዲስ መካከል በተደረገው ውል መሰረት የኦዲት ቡድኑ የኮንትራት ዋጋ መሻሻል እና የጊዜ መራዘምን በተመለከተ ለአማካሪ መሀንዲሱ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የፋብሪካ ግንባታው በዲዛይን ደረጃ በነበረበት ወቅት አንድ ጊዜ ማሻሻያ የተደረገለት መሆኑን ገልፀው በግንባታ ወቅት ከኮርፖሬሽኑና ከአማካሪው ካምፓኒ አቅም ውጪ በሆኑ ምክንያቶች በተቋራጩ በኩል የመዘግየት ችግሮች በመታየታቸው 7 ጊዜ የማሻሻያ ውል ሊፈርሙ የቻሉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

43. የስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ቅድመ- ጥናት ተደርጎላቸው አቅሙ ባላቸው ተቋራጮችና አማካሪዎች ካልተሰሩ፤ በታቀደ ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው በሀገሪቱ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንቅስቃሴ ፍጥነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ አገሪቷ ለሌላ ተግባር የምታውለውን በጀት ለሚታዘዙ ተጨማሪ ሥራዎች እንድታውል በማድረግ የሀገር ውስን ሀብትን ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

## ለሸንኮራ አገዳ ልማት እርሻ መሬት የመስኖ ጥናት እና ግንባታ

## በታቀደው ጊዜና በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ

44. ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚውል የመስኖ ግንባታን በታቀደው ጊዜና በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በማረጋገጥ ርክክብ ሊከናወን ይገባል፡፡

45. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚውል የመስኖ ግንባታን በታቀደው ጊዜና በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በማረጋገጥ ርክክብ የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የሸንኮራ አገዳ እርሻ ልማት ለማከናወን የመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ የወለንጪቲ ቦፋ መስኖ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እ.ኤ.አ ሰኔ 20/2010 ተጀምሮ በሶስት ዓመት ውስጥ እንዲጠናቀቅ የውል ስምምነት የተፈረመ ሲሆን፣ የኮንትራት መጠን ብር 799,394,202.51/ ሰባት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሁለት መቶ ሁለት 51/100/ ሆኖ ከውል ውጪ የተከፈለ ተጨማሪ ክፍያ የሌለ ቢሆንም፣ አራት ጊዜ የውል ማሻሻያ እና ሌሎች ተጨማሪ ንዑስ የውል ስምምነቶች ተፈርመው ሥራው እ.ኤ.አ ሰኔ 20/2013 መጠናቀቅ ሲገባው ለሁለት ዓመት ከሁለት ወር በመራዘሙ እስከ እ.ኤ.አ ነሀሴ 31/2015 የዘገየ መሆኑ ታውቋል፡፡

46. እንዲሁም በመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ አማካሪ ሆኖ የሰራው ድርጅት የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሲሆን የመነሻ ኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ጥር 1/2010 ለ 24 ወራት የሚያገለግል እና እንደ አስፈላጊነቱ የሚታደስ ሆኖ የመነሻ ኮንትራት ዋጋ ብር 17,427,728.99 ውል የፈረመ ቢሆንም፣ የመጀመሪያው የመነሻ ኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ሐምሌ 30/2012 የተጠናቀቀ በመሆኑ እና በመነሻ ኮንትራት ውል በተቀመጠላቸው ጊዜ ሥራዎች ባለመጠናቀቃቸው አራት ጊዜ ውሉ የታደሰ መሆኑ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- 1ኛ የማራዘሚያ ውል በዋናው ኮንትራት ውል ላይ የተመለከተውን የኮንትራት አስተዳደርና የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ሥራን /ሱፐርቪዥን/ ለመሥራት እ.ኤ.አ የ 12 ወራት ከነሀሴ 1/2012 እስከ ነሀሴ 31/2013 በብር 9,046,590 /ዘጠኝ ሚሊዮን አርባ ስድሰት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና/ 15% ቫትን ጨምሮ ውል የተገባ፣
- 2ኛ የማራዘሚያ ውል እ.ኤ.አ ከጥር 1/2013 እስከ ነሀሴ 31/2013 የኮንትራት አስተዳደርና የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር የሰው ሃይልና ተሽከርካሪ በማጠናከር ሥራውን ለ 8 ወራት ለመሥራት ብር 1,301,800 /አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ አንድ ሺህ ስምንት መቶ/15% ቫትን ጨምሮ ውል የተገባ፣
- 3ኛ የማራዘሚያ ውል ከለይ የተገለፀውን ተመሳሳይ ሥራ ለመሥራት ለ 12 ወራት እ.ኤ.አ ከመስከረም 1/2013 እስከ ነሀሴ 31/2014 የማራዘሚያ ዋጋ ብር 10,804,710

/አስር ሚሊዮን ስምንት መቶ አራት ሺህ ሰባት መቶ አስር/ 15% ቫትን ጨምሮ ውል የተገባ፣

- 4ኛ የማራዘሚያ ውል እ.ኤ.አ ከመስከረም 1/2014 እስከ ነሀሴ 31/2015 ለ 12 ወራት በመራዘሚያ ዋጋ 9,336,114/ዘጠኝ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ አንድ መቶ አስራ አራት/ 15% ቫትን ጨምሮ ውል የተገባ፣

  በድምሩ የአራት ጊዜ ውል መራዘም ብር 30,489,214/174.95%/ በመሆኑ ከመነሻ ዋጋ ተጨማሪ ክፍያ መከፈሉ ታውቋል፡፡

47. ስለ ሁኔታው በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ሲቪልና መስኖ መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ተቋራጩን በተመለከተ የክፍያ ማሻሻያ ሳይደረግ 4/አራት/ጊዜ የውል ማሻሻያ እና ሌሎች ተጨማሪ ንዑስ ስምምነቶች የተፈረሙበት ምክንያቶች፡-

   - ✓ የሚለማ መሬት ለውጥ በመኖሩ፣
   - ✓ የመስኖ ቴክኖሎጂ መረጣ ዲዛይን ለውጥ በመኖሩ፣
   - ✓ ለፋብሪካ ግብዓት የሚሆን ሸንኮራ አገዳ ቶሎ የሚደርስበት ሁኔታ ለማመቻቸት ለዋና ቦዩ/Main Cannal/ ቅርብ የሚሆኑ መልማት የሚችሉ ማሳዎች በማስፈለጉ እና
   - ✓ የወሰን ማስከበር ሥራዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የህዝብ መሰረተ ልማት የማይነኩ ማሳዎች በማስፈለጉ መሆኑን ሲገልፁ አማካሪ መሀንዲስን በተመለከተ ከመነሻ ኮንትራት የጊዜ መራዘም የተደረገበትምክንያት ሥራዎች በተመደበላቸው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው በመሆኑ ውሉ ለ 4/አራት/ ጊዜ ሊታደስ መቻሉን ገልፀዋል፡፡

48. ይሁን እንጂ ኃላፊው የተቋራጩ መነሻ ኮንትራት ዋጋ በገለጿቸው ምክንያቶችም ያልተሻሻለ መሆኑን በማስረጃ በመደገፍ ቢገልፁም፤ሥራው የጊዜ መራዘም በማሳየቱ ምክንያት በታቀደለት ወቅት ለታቀደለት ዓላማ እንዳይውል የተደረገ ከመሆኑም በላይ ለአማካሪ መሀንዲስ ተጨማሪ ክፍያ ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡

49. ለሸንኮራ አገዳ መሬት መስኖ ልማት የሚጠኑ ጥናቶች እና የሚነደፉ ዲዛይኖች ጊዜ ተሰጥቷቸው ሊጠኑ እና ሊነደፉ የሚገባ ሆኖ፤ ተቋራጮችና አማካሪዎች በአሰሪው መ/ቤት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች በእቅድ በተያዘ ፕሮግራም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በታቀደ ጊዜ እና በተመደበ በጀት እንዲያጠናቅቁ ካልተደረገ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ አገሪቷ ለሌላ ተግባር የምታውለውን በጀት ለሚታዘዙ ተጨማሪ ሥራዎች እንድታውል በማድረግ የሀገር ውስን ሀብትን ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

## የሸንኮራ አገዳ ልማት መሬት ርክክብ፣ የማሽነሪ አቅርቦት እና የመሬት ዝግጅት እና የእርሻ ሥራ/ኦፕሬሽን/ በተመለከተ

50.ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት የመሬት ርክክብ ሊፈፀም፣የማሽነሪ አቅርቦት እንዲሟሉ ሊደረግ፣ ለአገዳ ልማቱ የመሬት ዝግጅት የማለስለስ/Fine Level/ ሥራ ሊደገፍ፤ እንዲሁም የእርሻ ኦፕሬሽን ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

51.ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት የመሬት ርክክብ መፈፀሙን፣የማሽነሪ አቅርቦት እንዲሟሉ ያደረገ መሆኑን እና ለአገዳ ልማት የመሬት ዝግጅት/Fine level/ ሥራን መደገፉን፤እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፤

**የሸንኮራ አገዳ ልማት መሬት ርክክብና ዝግጅት**

- በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ከ2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን እቅድ አፈፃፀም የሸንኮራ አገዳ ልማት መሬት ርክክብ በማድረግ የፕሮጀክት አገዳ ተከላ/ከአዲሱ ገበሬ ማህበር/ 1,090 ሄክታር ለመትከል ታቅዶ ክንውኑ 277.52/25%/ ሄክታር መሆኑ ታውቋል፡፡

52.ስለሁኔታው የእርሻ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ለፕሮጀክት ሸንኮራ አገዳ ተከላ እቅድ አፈፃፀም ማነስ ምክንያት የመስኖ መሰረተ ልማት አለመዘርጋት ሲሆን፤በወቅቱ የነበሩ ኮንትራክተር/ኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች/ እና አማካሪ ድርጅት/ፌዴራል ውሃ ሥራዎች/ የተገለፀውን መሰረተ ልማት ባለማሟላታቸው ሲሆን፤ በተጨማሪም ሥራው ሲጀመር የአዋጭነት ጥናት ቀርቦ ሁሉም የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተወያይተውበት የጋራ አቋም ተይዞ በጥናትና በፕሮግራም የተገባበት ፕሮጀክት ባለመሆኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

53. ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚሆኑ ማሳዎች በየዓመቱ በታቀደላቸው መሰረት ዝግጅት ተደርጎላቸው ርክክብ በመፈፀም አለመተከላቸው ፋብሪካውን በአንድ ወቅት የግብዓት እጥረት እንዲያጋጥመው ከማድረጉም ባሻገር አድሜያቸው ያልደረሱ ማሳዎችን እንዲቆረጡ የሚደረስበት ሁኔታ ሊያደርስ ወይም ፋብሪካው እንዲቆም የሚገደድበት ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበት ደረጃ የሚያደርስ ይሆናል፡፡

**የማሽነሪ አቅርቦት**

54.በ2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 5,990.35 ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማሳ ላይ ማዳበሪያ መስጠት ታቅዶ አፈፃፀሙ 3,499/58%/ ሆኖ፤ በማሽነሪ ማዳበሪያ 4,065 ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማሳ ላይ ለመስጠት ታቅዶ ክንውኑ 1,683.38 ሄክታር ሲሆን፤በሰው ሃይል ማዳበሪያ መስጠት 6,512.75 ሄክታር ለመሸፈን ታቅዶ አፈፃፀሙ 3,201.88 ሄክታር/49%/ መሆኑ ሲታወቅ የፋብሪካ ተረፈ ምርትን/Filter Cake/ 27,000 ቶን/ሄክታር ለመጠቀም ታቅዶ ክንውኑ

10,498.2/39%/ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑ በ 2008 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ተመልክቷል፡፡

55. ስለሁኔታው የእርሻ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በ 2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን በማሽነሪ ማዳበሪያ መስጠትን በተመለከተ አፈፃፀሙ ሊወርድ የቻለበት ምክንያት የዩሪያ ማዳበሪ አቅርቦት አለመኖር ሲሆን፤ ይህም በተለያዩ ጊዜያቶች በገንዘብ እጥረት ምክንያት ግብዓቱ በወቅቱ ባለመገዛቱ በመሆኑ እስከ የኦዲቱ ቃለ-መጠይቅ የቀረበበት እ.ኤ.አ 07/11/2016 ድረስ መፍትሄ ያላገኘ ችግር መሆኑን አብራርተው የፋብሪካ ተረፈ ምርትን ከመጠቀም አንፃር ከፍተኛ ችግር የሆነው ከትራንስፖርት ጋር በተያያዘ ሲሆን፤ ፋብሪካው ይህንን ግብዓት ከሚፈለጉ ማሳዎች በአማካይ 14/አስራ አራት/ ኪሎሜትር እርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ በእስታንዳርዱ መሰረት አጓጉዞ ለመበተን የማሽነሪ እጥረት በመኖሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

56. የአገዳ ተክሉን በማፋፋት የሸንኮራ አገዳ ጁስ ይዘቱ/ሱክሮስ/ን የሚጠብቁ ዩሪያ ማዳበሪያና የፋብሪካ ተረፈ ምርት ማዳበሪያ በተፈለገው መጠን አለመስጠት ፋብሪካው ማምረት የሚችለውን የስኳር ምርት መጠን ማምረት የማያስችለው በመሆኑ በስኳር ምርት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ምንጭ በማሳጣት ለኪሳራ ይዳርጋል፡፡

**የእርሻ ሥራ ኦፐሬሽን**

57.በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ከ 2007 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በ 2,278 ሄክታር የአገዳ ማሳ ላይ የኬሚካል ርጭት በማድረግ የበሽታና ተባይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ግኘው በመዘግየቱ 771.38/34%/ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ተክል ላይ ርጭት መከናወኑ ሲታወቅ፤ የፕሮጀክት የሸንኮራ አገዳ ምርትን 9.5 ቶን/ሄክታር/ወር ለማድረስ ታቅዶ ክንውኑ 5.5/58%/ መሆኑ ታውቋል፡፡

58.እንዲሁም በ 2007 በጀት ዓመት ስኳር ፋብሪካው በስሩ በሶስት ደረጃ ተከፍለው ከሚገኙ ከድርጅቱ የአገዳ ማሳ 3,789.79 ሄክታር ለመቁረጥ ታቅዶ ክንውኑ 3,699 ሄክታር/98%/፣ ከገበሬ ማህበር 2,831.95 ሄክታር ለመቁረጥ ታቅዶ ክንውኑ 2,567/91%/ ሄክታር ሆኖ ከፕሮጀክት ማሳ 1,564.23 ሄክታር ለመቁረጥ ታቅዶ ክንውኑ 7,41/46%/ ሄክታር መሆኑ ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ መረዳት የተቻለ ሆኖ ለፋብሪካ የቀረበ አገዳን በተመለከተ ከድርጅቱ ማሳ 565,904.1 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንውኑ 445,232/79%/ ቶን፣ ከገበሬ ማህበር ማሳ 462,351.9 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንውኑ 362,241 ቶን ሲሆን፤ ከፕሮጀክት 273,288.7 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንውኑ 98,617/36%/ ቶን መሆኑ ታውቋል፡፡

59. ስለሁኔታው የእርሻ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የኬሚካል ርጭትን በተመለከተ የበሽታና የተባይ አስፈላጊ ግብዓቶች የእቅዱ ዘመን ከመድረሱ ስድስት ወር በፊት ለግዥ ክፍል የሚቀርቡ ቢሆንም፤ ድርጅቱ ከ 2006 በጀት

ዓመት ወዲህ ከገንዘብ እጥረት ጋር ተያይዞ ክፍያዎችን መፈፀም ባለመቻሉ አቅርቦቱ ሊዘገይ በመቻሉ መሆኑን ገልፀው በአገዳ ተክሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ውሃን በብዘትና በድግግሞሽ የማጠጣት አማራጭ መጠቀም የተቻለ መሆኑን ገልፀው በ 2007 በጀት ዓመት የአገዳ ቆረጣና አቅርቦት ሥራዎች አፈፃፀም በተለይም በፕሮጀክቱ በኩል ዝቅተኛ ሊሆን የቻለው በማሽነሪ እጥረት ምክንያት ሲሆን በድርጅቱና በኮርፖሬሽኑ ችግሩ ታምኖበት በኮሚቴ እንዲጠና በወቅቱ የተወሰነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

60. ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚሆኑ ማሳዎች በየዓመቱ በታቀደላቸው መሰረት ዝግጅት ተደርጎላቸው አለመተከላቸው ፋብሪካውን በአንድ ወቅት የግብዓት እጥረት እንዲያጋጥመው ከማድረጉም ባሻገር አድሜያቸው ያልደረሱ ማሳዎችን እንዲቆረጡ የሚደረስበት ሁኔታ ሊያደርስ ወይም ፋብሪካው እንዲቆም የሚገደድበት ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበት ደረጃ የሚያደርስ ሲሆን፤ ለተተከሉ የሸንኮራ አገዳ ማሳዎችም ቅድመ-ዝግጅት በማድረግ የተባይና የበሽታ መከላከል ሥራ አለመሥራት ፋብሪካው ማምረት የሚችለውን የስኳር ምርት መጠን ማምረት የማያስችለው በመሆኑ በስኳር ምርት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ምንጭ በማሳጣት ለኪሳራ ይዳርጋል፡፡

## ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት

## አሰጣጥና ሀብትን አዛውሮ መጠቀምን በተመለከተ

61. ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር ሊደረግ፤እንዲሁም ሀብትን በማዛወር የማሽነሪ፣ የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ በመስጠት ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ ግብዓቶች በወቅቱ እንዲቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡

62. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት የተገበረ እና ድጋፍ የሰጠ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለፋብሪካ አገልግሎት ሊውል የታሰበ አዲስ ወርክ ሾፕ የተጀመረ ሆኖ በአካል ቢታይም፤ ተቋራጩ ሥራውን ያቋረጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

63. በተጨማሪም በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ከ 2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን ከመስክ ጥገና እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መመልከት እንደተቻለው ለእርሻ ክፍል የሚሆኑ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች፡-

- ከባድ ጥገና/Over-haul maintenance/ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ 18 ታቅዶ አፈፃፀሙ በመለዋወጫ እጥረት 9 መሆኑ፣
- ሰርቪስ/Planned maintenance/ በበጀት ዓመቱ በቁጥር 637 ለመሥራት ታቅዶ በመለዋወጫ እጥረት 457 መሆኑ፣
- አነስተኛ ፈረስ ጉልበት ያላቸው የጆንዲር ትራክተሮች መለዋወጫ አለመቅረብ/ሞጆ ደረቅ ወደብ ደርሰው በብር እጥረት ምክንያት መያዝ/፣

- የሸንኮራ አገዳ ወደ ፋብሪካ ማጓጓዣ ጋሪ እጥረት፣ እንዲሁም የአገዳ ጋሪ ጎማ ክምችት በመጋዘን አለመኖር ችግሮች የተስተዋሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

64.እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ የማሽነሪ፣የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ ሀብትን አዛውሮ በመጠቀም ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ ግብዓቶችን በወቅቱ እንዲቀርቡ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የአገዳ አቅርቦትን በተመለከተ ከ 2007 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም መረዳት እንደተቻለው ከፕሮጀክት የአገዳ ማሳ ላይ 1,564.23 ሄክታር ለመቁረጥ ታቅዶ ክንውኑ 7,41/46%/ ሄክታር ሲሆን፣ ለፋብሪካው ከፕሮጀክት 462,351.9 ቶን አገዳ ለማቅረብ ታቅዶ አፈፃፀሙ 98,617/36%/ መሆኑ ሲታወቅ ለ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆን አስተዋፆ ያደረጉ የማሽነሪ አቅርቦት ችግር እና የፋብሪካው በብልሽት/ቴክኒካል ችግር/ መቆም መሆኑ ታውቋል፡፡

65.ስለ ሁኔታው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የግዥ ቡድን መሪና የእርሻ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የግዥ ቡድን መሪው በወቅቱ ግዥ ለመፈፀም ያልተቻለበት ምክንያት የውጭ ምንዛሪ ፍቃድ የሚጠይቀው እና የሚያስፈቅደው ኮርፖሬሽኑ በመሆኑ በተፈለገው መጠን እና ጊዜ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ባለመቻሉ ሲሆን፣ ተገዝተው ገብተው በየወደቡ የደረሱትንም እቃዎች ለማንሳት የሚያስችል ገንዘብ ማግኘት ባለመቻሉ መሆኑን አብራርተው ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ ግብዓቶችን በተመለከተ የማሽነሪ አቅርቦት ችግር በማጋጠሙ የእቅድ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሊሆን የቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

66.ለእርሻ የሚሆኑ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎችን እና መለዋወጫዎቻቸውን በየእቅድ ዓመቱ በሚፈለገው መጠን አለማቅረብ ለስኳር ፋብሪካው ግብዓት ማቅረብ የማያስችል በመሆኑ በየዓመቱ ለማምረት የሚታቀደውን የስኳር ምርት መጠን ማምረት የማያስችል ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱ የህዝቦቿን ፍላጎት ለመደጎም ስኳር ከውጭ እንድታመጣ በማድረግ ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል፡፡

## ዘመናዊ ጥገናና እድሳት እና የማሽነሪና ግብዓት አቅርቦት ለፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀም የሚያበረክተውን አስተዋፆ በተመለከተ

67.ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ዘመናዊ የማሽነሪ ጥገናና እድሳት ስርዓት በመዘርጋት አጠቃላይ የፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀም 90% የደረሰ መሆኑን በማረጋገጥ አጠቃላይ የፋብሪካ የጊዜ አጠቃቀም ከ 87% እንዳይወርድ ድጋፍ ሊሰጥ፣እንዲሁም የማሽነሪ እና የግብዓት አቅርቦት ድጋፍ ከምርት እቅድ ጋር የተጣጣመ በማድረግ በግብዓት ምክንያት የሚፈጠር የሥራ መቆምን/Down Time/ ወደ ዜሮ እንዲወርድ ሊደረግ ይገባል፡፡

68. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ዘመናዊ የማሽነሪ ጥገናና እድሳት ስርዓት ዘርግቶ አጠቃላይ የፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀም/Over all time efficiency/ 90% መድረሱን የተከታተለና የፋብሪካ የጊዜ አጠቃቀም ከ 87% በታች እንዳይወርድ ድጋፍ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ በ 2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 85% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 68.61% ሲሆን በ 2008 በጀት ዓመት 82.8% ታቅዶ አፈፃፀሙ 57.6% በመሆን ከ 87% በታች መውረዳቸውን ከ 2007 እና 2008 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማወቅ ተችሏል፡፡

69. እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ የማሽነሪ እና የግብዓት አቅርቦት ድጋፍን ከምርት እቅድ ጋር የተጣጣመ በማድረግ በግብዓት ምክንያት የሥራ መቆምን/Down-Time/ ወደ ዜሮ እንዲወርድ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ❖ በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ በ2006 በጀት ዓመት የምርት ዘመን ፋብሪካው 1,022,265 ኩንታል ስኳር ለማምረት አቅዶ 806,655/78.9%/ ኩንታል ስኳር 215,610/21.1%/ ኩንታል በማነስ ያመረተ መሆኑ ሲታወቅ፤ ምክንያቶቹም፡-
    - የፋብሪካ የፕሮጀክት ሥራዎች አለመጠናቀቅ፣
    - ለምርት መጨመር ዓይነተኛ አስተዋፆ ያለው የኮንቲኒየስ ፓን/በውስጡ ማቀዝቀዣ ያለው ስኳርን የሚያቀዘቅዝ/ ሥራ አለመጀመር እና የዲዛይን ችግሮች፣
    - ፋብሪካው በሳይረፕ አውትሌት/የስኳር ጁስ ማስወጫ/ ዲዛይን ችግር መቆም፣
- ፋብሪካው በአጠቃላይ በውስጣዊና ውጪያዊ ምክንያቶች 1,434.5 ሰዓታት ሳያመርት መቆሙ ታውቋል፡፡
- ✓ በ 2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 1,548,860 ኩንታል ስኳር ለማምረት ታቅዶ አፈፃፀሙ 1,109,669.3/71.6%/ ኩንታል ሆኖ በ 439,190.7/28.4%/ ኩንታል በማነስ የተመረተ መሆኑ፣
- ለዚህም ዋና ችግሮቹ የመለዋወጫዎች በወቅቱ አለመቅረብ ሲሆን ለማሳያ የጁስና የሳይረፕ ሰልፋይተር አቋራጭ ቱቦዎች መበላት፣
- የግሬደር ሲቭ /የስኳርን አንኳር ለመለየት የሚያገለግል ወንፊት/ አለመኖር፣
- ከወፍጮ ክፍል ገለባ/ባጋስ/ ተቀብሎ ወደ ቦይለር/የእንፋሎት ሃይል ማመንጫ ክፍል የሚያጓጉዝ ተሸካሚ/Main Bagasse elevator Drive gear box/ መሰበር
- በበጀት ዓመቱ 15 ሰዓት የማምረቻ ጊዜ ሊባክን ይችላል ተብሎ ቢታቀድም ወደ 31.9 ሰዓት ከፍ ያለ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ✓ በ 2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 1,328,200 ኩንታል ለማምረት ታቅዶ አፈፃፀሙ 934,294.5/70.34%/ ሆኖ 393,905.5/29.66%/ ኩንታል በማነስ የተመረተ መሆኑ፤ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከፋብሪካ ችግር ጋር በተያያዘ ፋብሪካው ለ 112 ሰዓት የቆመ ሲሆን፤ ምክንያቶቹ፡-
- በአሮጌው ስኳር ፋብሪካ የወፍጮ ማስነሻ/MCC Gear box/ ፋብሪካው በአነስተኛ አቅም እንዲጀምር በመደረጉ፣
  - ➢ በእንፋሎት ሃይል ማመንጫ ውስጥ የሚገኝ/I.D Fan ,V.F.D/ካርድ መበላሸት፣
  - ➢ የቢ እና ሲ ዓይነት ስኳር ማቅለጫ/ B and C sugar type melter/ መበላሸት እና
  - ➢ የሸንኮራ አገዳ መከርተፊያ/Fiberizer hammer/ መለዋወጫ አለመኖር፣መሆኑ ታውቋል፡፡

70.ስለ ሁኔታው በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የፋብሪካ ኦፕሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ለ 2006 በጀት ዓመት የምርት ዘመን በ 2005 በጀት ዓመት አዲሱ ፋብሪካ ለ 67 ቀናት ብቻ የሙከራ የማምረት ሂደት ያከናወነ በመሆኑ ከማሽነሪዎች ጥገና ጉድለት ጋር በተያያዘ ለኮርፖሬሽኑ የቀረበ የድጋፍ ጥያቄ አለመኖሩን ገልፀው በ 2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን ችግር እንዳይገጥም የኬን ቴብል ሻፍት/የአገዳ መቀበያውን የሚያንቀሳቅስ/ ችግር እንዲወገድ ፋብሪካውን ለተከለው ካምፓኒ ተነግሮ እንዲስተካከል የተደረገ መሆኑን፤ እንዲሁም ወንፊቶች እንዲገቡ ሲደረግ የኤምሲሲ/MCC Gear box/ የግዥ ትዕዛዝ እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን፤ በ 2008 በጀት ዓመት ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ጥረት ተደርጓል የ ኤምሲሲ ጊር ቦክስ/ወፍጮ ማስነሻ/ ክትትል እየተደረገ ባለበት ወቅት አነስተኛ አቅም ባለው የቀድሞው ፋብሪካ ጊር ቦክስ ሥራ እንዲጀመር የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

71.የፋብሪካው ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ይህን ቢሉም ከ 2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት በነበረው የፋብሪካው የሥራ ሂደት ወቅት ከላይ በእያንዳንዱ በጀት ዓመት በተገለፁት ችግሮች ምክንያት ፋብሪካው በእቅድ የተያዘለትን ምርት ማምረት ያልቻለ መሆኑ በእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶቹ ላይ ተመልክቷል፡፡

72.በስኳር ኮርፖሬሽን የግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር ከምርት እቅድ ጋር የተጣጣመ የግብዓት አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ እና በግብዓት አቅርቦት ምክንያት የሚፈጠርን የሥራ መቆም/Down Time/ ዜሮ ማድረግ፤ እንዲሁም ለስኳር ፋብሪካዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣ ክትትል ማድረግና መቆጣጠር ከሚለው አንፃር የክትትል እና ቁጥጥር መርሀ-ግብር በመዘርጋት የመለዋወጫ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ባለመደረጉ ምክንያት የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በየበጀት ዓመቱ የታቀደለትን የምርት መጠን እንዲያመርት አቅም ያልተገነባለት ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱ ልታገኝ የምትችለውን ገቢ እንድታጣ ምክንያት ይሆናል፡፡

## ግዥዎች ተጠያቂነት ባለው አግባብ የሚፈፀሙ መሆኑን በተመለከተ

73.ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ውጤታማነት፣ ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በአግባቡ ሊፈፀሙ ይገባል፡፡

74. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ውጤታማነት ግዝዎችን ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት፣እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆኑ መልኩ መፈፀማቸውን ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ከ 2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መመልከት እንደተቻለው ለእርሻ ክፍል የሚሆኑ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ፡-

- ኮርፖሬሽኑ የመለዋወጫ ችግርን ድጋፍ የተጠየቀበት የተለያዩ ደብዳቤዎችን መመልከት የተቻለ ቢሆንም ለማሳያ ጷጉሜ 2 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር 07/0/0298/1.1.5 ለወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ አገዳ ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ 26/ሃያ ስድስት/ የቤል ትራክተሮች መለዋወጫ እቃዎች ለክረምት ጥገና ወቅት እንዲያገለግል በአፋጣኝ ከውጭ ሀገር በአውሮፕላን እንዲመጣ የተጠየቀበት እና ነሀሴ 19 ቀን 2007 ዓ.ም ጅቡቲ ወደብ ተከማችተው የሚገኙ የፋብሪካ እቃዎችን በተመለከተ 5 ኮንቴይነር እቃዎች ወደ ሀገር በዋት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር እንዲገቡ ድጋፍ የተጠየቀባቸው መፍትሄ ያላገኙ ደብዳቤዎች ቀርበው ለማየት ተችሏል፡፡/ውጤታማነት/

75. በተጨማሪም ህዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር 29/266/1.1.5 ለስኳር ኮርፖሬሽን በተፃፈ ደብዳቤ ከሞጆ ደረቅ ወደብ ለሚመጡ እቃዎች የገንዘብ ጥያቄን አስመልክቶ ብር 22,019,678.78/ሃያ ሁለት ሚሊዮን አስራ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ስምንት 78/100/ መክፈል ባለመቻሉ የመወረሻ ጊዜያቸው የተቃረቡ 9 እቃዎች ያሉ መሆኑ ታውቋል፡፡/ተጠያቂነት/

76. እንዲሁም የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በ 2007 በጀት ዓመት ወደብ የደረሱ እቃዎችን ወደ ፋብሪካ አጓጉዞ ለመውሰድ ባለመቻሉ ለኮንቴይነር ዲሚሬጅ/በወቅቱ ባለማንሳት የሚከፈል ክፍያ/ እና ለመጋዘን ኪራይ ብር 393,231.33 የከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡/ወጪ ቆጣቢ/

77.የመስክ መሳሪያዎች ጥገና መለዋወጫ ግዥ እና በውጪ ኩባኒያ በኩል የተደረገ ጥገናን በተመለከተ፡-

- የኤክስካቫተር ግዥ መጠይቅ ቁጥር 0745 እና የዶዘር ግዥ መጠይቅ ቁጥር 0653 በአስመጪው ኩባኒያ በኩል እንዲጠገን ክፍያ የተፈፀመ ቢሆንም፣መለዋወጫ ከውጪ ሊያመጡ ባለመቻላቸው ሥራ ላይ ችግር መፍጠሩ፣

- ገደብ ኢንጅነሪንግ ሞዴላቸው 9330፣ 9410 የተባሉ ጆንዲር ትራክተሮችን ለድርጅቱ ካስመጣ በኋላ በ EI-157495 እና PR-803 የተጠየቁ የሰርቪስ እቃዎች/ቺንጋ፣ ሬጉሌተር፣ ቴንሽነር/ የመሳሰሉትን ባለማቅረቡ ሥራ ላይ ችግር መፍጠሩ፣
- በኮርፖሬሽን በኩል ተገዝቶ የቀረበው ቨርሳታይል አርቲኩሌትድ ትራክተር ሰርቪስ ኪት/መገጣጠሚያ እቃዎች/ አብሮ ባለመገዛቱ ሥራ ላይ ችግር የፈጠረ መሆኑ፣
- በቁጥር ሁለት ጆንዲር ትራክተሮች በጊር ቦክስ ብልሽትና ካም ሻፍት ሴንሰር ምልክት አብርቶ የቆሙ ሲሆን በዋስትናው መሰረት እንዲጠገን ህዳር 28/2006 በቁጥር 01/0286/1.1.5 በድርጅቱ በኩል ደብዳቤ ቢፃፍም መልስ ያልተገኘ በመሆኑ ከላይ የተመለከቱት ችግሮች በመሳሪያ ጥገና ክፍሉ የደረሱ መሆናቸው ታውቋል፡፡

78. ስለ ሁኔታው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የግዥ ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ችግሮች የተከሰቱት ኮርፖሬሽኑ ካለበት የፋይናንስ እጥረት የተነሳ የሚመስላቸው መሆኑን ገልፀው የኮርፖሬሽኑ ድጋፍ አሰጣጥ አለመሟላት ምክንያትን በተመለከተ ያላቸው ድርሻ ውስን በመሆኑ ለመግለፅ የሚቸገሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

79. በስኳር ኮርፖሬሽን ኮርፖሬት ፋይናንስ ከተሰጠው ተግባር የፋብሪካዎችንና የፕሮጀክቶችን የፋይናንስ አቋም ትንተና በማካሄድ መገምገም፣የሚካሄዱት ኢንቨስትመንቶች በታቀደላቸው ጊዜና ወጪ መካሄዳቸውን ማረጋገጥ የሚል ከመሆኑ አንፃር ኮርፖሬቱ ለፋብሪካው ወሳኝ ግብዓት የሆኑ እቃዎች ወደ መወረስ ደረጃ እስኪደርሱ ክፍያ ያልፈፀመበት ምክንያት የሥራ ግዴታን አለመወጣቱን ከማመልከቱም በላይ ከፍተኛ ወጪ ተከፍሎባቸው ወደ ሀገር የገቡ እቃዎች በመወረስ ምክንያት ለታቀደላቸው ዓላማ እንዳይውሉ ከማድረጉም በላይ ለከፍተኛ የሀብት ኪሳራ ይዳርጋል፡፡

80. እንዲሁም በስኳር ኮርፖሬሽን ኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት ከተሰጠው ተግባር የፋብሪካዎች፣ የፕሮጀክትና የዋናውን መ/ቤት የግዥ ፍላጎት በመለየትና በጋራ በመግዛት ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ የሚል በመሆኑ ስኳር ፋብሪካው መለዋወጫ እጥረት በገጠመው ወቅት መፍትሄ ለማግኘት በማስረጃ ድጋፍ በጠየቀበት ጊዜ የኮርፖሬት ግዥ ክፍሉ የመፍትሄ አካል ባለመሆኑ ምክንያት ድርጅቱ በአፋጣኝ የአገዳ ጎታች ጋሪዎችን ባለማግኘቱ ለፋብሪካው የየቀን ተፈላጊ የአገዳ አቅርቦት ማቅረብ ባለመቻሉ በስኳር ምርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ የተፈፀሙ ግዥዎችን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለፈላጊው ክፍል በወቅቱ ሥራ ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ ኃላፊነትን አለመወጣት ከመሆኑም ባሻገር የሥራ ክፍሎች በበጀት ዓመት እቅድ የያዙትን መሥራት እንዳይችሉ በማድረጉ በፋብሪካው ምርት ሂደት ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## ዓመታዊ የንብረት ቆጠራን/Inventory/ን በተመለከተ

81.በንብረት ቆጠራ ወቅት የታዩ ልዩነቶች የንብረት መዝገቡ፣ የእቃዎች መቀበያ ሰነድ፣በእቃ መጠየቂያ እና በእቃ ማውጫ ሰነድ እና በትክክለኛው ቀሪ ክምችት መካከል ተገቢው ማጣራት ተከናውኖ ልዩነቶች ከተረጋገጡ በኋላ በገበያ ዋጋ መሰረት ተሰልቶ እንዲከፈል ወይም ንብረቱ እንዲተካ ሊደረግ ይገባል፡፡

82.ኮርፖሬሽኑ በንብረት ቆጠራ ወቅት የታዩ ልዩነቶች የንብረት መዝገቡ፣ የእቃዎች መቀበያ ሰነድ፣ በእቃ መጠየቂያና በእቃ ማውጫ ሰነድ እና በትክክለኛው ቀሪ ክምችት መካከል ተገቢው ማጣራት ተከናውኖ ልዩነቶች ከተረጋገጡ በኋላ በገበያ መሰረት ተሰልቶ እንዲከፈል ወይም ንብረቱ እንዲተካ ያስደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-በ 2014/2015 በጀት ዓመት በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በተደረገ ንብረት ቆጠራ/Inventory/፡- ቀላል ተሽከርካሪዎች በቁጥር ብዛታቸው 124 የሆኑ እና ከባድ ተሽከርካሪዎች ብዛታቸው 41 የሆኑ ያልተገኙ መሆናቸውን ከቆጠራው ሰነድ መረዳት ተችሏል፡፡ ለማሳያ ከቀላል ተሽከርካሪዎች፡-

1. የዴው ገልባጭ /Daewoo Dump truck/ የንብረት መለያ ቁጥር /Property no./ 3- 36859 የተገዛበት ዓመት እ.ኤ.አ /Year of Purchase/ 2007/2008 የነበረበት ክፍል /Location R.o Project/ የተገዛበት ዋጋ/unit price/ ብር 585,747.26
2. ሚስትቡሽ /Mitsubishi Single Cabine Pick-up/ የንብረት መለያ ቁጥር /Property no./ 3- 08213 የተገዛበት ዓመት እ.ኤ.አ /Year of Purchase 1999/2000/ የነበረበት ክፍል ሲቪል መሀንዲስ /Location Civil Works/ የተገዛበት ዋጋ /unit Price /ብር 126,724.69
3. ካቻ ማሊ አውቶቢስ /Cachamale Bus A 120 E 18 /IVECO/የንብረት መለያ ቁጥር/Property no. 4-28747/ የተገዛበት ዓመት እ.ኤ.አ /Year of Purchase 1997/1998 / የነበረበት ክፍል እርሻ/Location L.P.C.D/የተገዛበት ዋጋ /Unit Price/ብር 427,258.67

83.እንዲሁም በ 2015/2016 በተደረገ ቆጠራ 172 ቀላል እና 21 ከባድ ተሽከርካሪዎች ያልተገኙ መሆኑ ከቆጠራ ሰነዱ ታውቋል፡፡

84.በተጨማሪም በ 2014/2015 በድርጅቱ በተደረገ ቆጠራ ወቅት 12 ተሽከርካሪዎች:- ከሰም/ 2/፣ ለትምህርት ቢሮ በስጦታ የተሰጠ/2/፣አዲስ አበባ/1/፣ ለዩኒየን በስጦታ የተሰጠ/1/፣ መተሀራ/3/፣ ኩራዝ/1/ እና ተንዳሆ/2/፤ እንዲሁም 2015/2016 ቆጠራ ወቅት አዲስ በባ/7/፣ ከሰም/2/፣ መድህን/1/ ፣ለትምህርት ቢሮ/2/፣ ናዝሬት/1/ ፣ ለዩኒየን በስጦታ የተሰጠ/1/ ፣ ደብረዘይት/4/፣ መተሐራ/3/ ፣ኩራዝ/1/ ፣ተንዳሆ/2/፣ ፊንጫ/1/ እና በላይ አብ/1/ የሚገኙ መሆኑን ከቆጠራ ሰነድ መረዳት የተቻለ ሲሆን፤ከላይ የተገለፁት ተሽከርካሪዎች በስጦታ፣በውሰትም ሆነ በተለያዩ

ምክንያቶች በተጠቀሱት ቦታ ስለመገኘታቸው በስኳር ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር የሚታወቁ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

85.በወንጂ ስኳር ፋብሪካ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ከውስጥ ኦዲት ሪፖርት መመልከት እንደተቻለው በሲቪል መሀንዲስ ቡድን ስር የሚገኙ በናሙና በታዩ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች እ.ኤ.አ ከጥር 2014 እስከ ታህሳስ 2014 ባሉት ጊዜያት በተቀመጠላቸው በጀት ሬት ሊጠቀሙ የሚገባቸው የነዳጅ መጠን 86,683 ሊትር ሆኖ ሳለ የተጠቀሙት የነዳጅ መጠን 138,585 ሊትር ሆኖ 51,902 ሊትር ከበጀት ሬት በላይ ተጠቅመው መገኘታቸው ከሪፖርቱ መረዳት ተችሏል፡፡

86.ስለ ሁኔታው የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የ 2014/2015 በጀት ዓመት ቆጠራን በተመለከተ 3-08253 እና 3-36859 ከሚገለሉት ተሽከርካሪዎች ውስጥ መሆናቸውን፣ 4-28747 የሚባል ተሽከርካሪ የሌላቸው መሆኑን እና 124 ከባድ ተሽከርካሪዎች በቆጠራ ሰነድ አልተገኘም ለሚለው ከቆጠራ ኮሚቴ አያዝ ችግር ካልሆነ በስተቀር ተሽከርካሪዎቹ የነበሩ መሆናቸውን እና የመድህን ሽፋን እንዲኖራቸው የተደረገ መሆኑን ገልፀው በ 2015/2016 ለተደረገው ቆጠራ መልስ ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

87.በ2014/2015 እና 2015/2016 እ.ኤ.አ በጀት ዓመት ቆጠራ በተከናወነበት ወቅት ተሽከርካሪዎች በተለያዩ ቦታ መገኘታቸውን እና በስጦታ መሰጠታቸውን በተመለከተ በውሰት የተሰጡት ተሽከርካሪዎች ህጋዊ ትዕዛዝ ፣ ደብዳቤና የመውጫ ሰነድ ያላቸው ሲሆን፤ አዲስ አበባ አሉ የተባሉ 7/ሰባት ተሽከርካሪዎች/ ተጠግነው የወጡና ሥራ ላይ ያሉ 3-37063፣ 3-29218፣ WT-0120፣ WT-0124 እና WT-0132 ሆነው በጥገና ሂደት ላይ ያሉ በአዲስ አበባ ያሉ 3-37062 እና 3-37067 ሲሆኑ በናዝሬት 1 በመድህን 1 አሉ ለተባሉት ታርጋቸው ስላልተጠቀሰ ማብራሪያ ለመስጠት የተቸገሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

88.ነዳጅን በተመለከተ በሰጡት መልስ ማንኛውም የድርጅቱ ተሽከርካሪ የቀን ራሽን እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን ከተፈቀደለት በላይ እንዳይሰጥ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን፤ ሆኖም ግን ተሽከርካሪውን የሚያስተዳድረው ክፍል ተጨማሪ ሥራሲያጋጥመው በኩፖን በሥራ አስኪያጅ ተፈርሞ ሰነዱ ሲቀርብ ነዳጅ ከራሽን ውጪ የሚሰጥበት አሰራር ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

89.የንብረት አስተዳደር የቡድን መሪው ይህን ይበሉ እንጂ ከላይ በኦዲት ቡድኑ የቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የድርጅቱን የቆጠራ ሰነድ በመመልከት በመሆኑ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተሟላ ታሪኩ ተመዝግቦለት የሚታይ በመሆኑ የታርጋ ቁጥር ባለማወቃችን መልስ ለመስጠት እንድንቸገር አድርጎናል ለሚለው የኦዲት ቡድኑ የማይቀበለው ሲሆን፤ከላይ በዝርዝር መልስ የተሰጠበትም ቢሆን በማስረጃ ተደግፎ ባለመቅረቡ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

90.በስኳር ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ተግባር የተቀናጀ ውጤታማና ችግር ፈቺ ስርዓት በመዘርጋት ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ የንብረት አስተዳደር ማከናወን ቢሆንም ከዚህ አኳያ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ባለመሰራቱ በዓመታዊ ቆጠራ ወቅት ለሚታዩ ልዩነቶች ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ የመንግስት ንብረት ለምዝበራ እና ለስርቆት እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡

### በመመሪያ መሰረት መወገድ የሚገባቸው ንብረቶችን በተመለከተ

91.በእርጅ እና በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የስኳር ፋብሪካዎች ቋሚ ንብረቶች በኮርፖሬሽኑ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በአስወጋጅ ኮሚቴ ተጣርተው ለውሳኔ ቀርበው እንዲወገዱ ሊደረግ ይገባል፡፡

92. ኮርፖሬሽኑ በእርጅና እና በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የነባር ፋብሪካዎች ቋሚ ንብረቶች በኮርፖሬሽኑ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በአስወጋጅ ኮሚቴ ተጣርተው ለውሳኔ ቀርበው የተወገዱ ስለመሆናቸው ክትትል ስለማድረጉ ኦዲት ሲደረግ በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ አጠቃላይ ብዛታቸው 24,785/obsolete Items/ ሆኖ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 43,865,217.16 ሲሆን ያልተወገዱ መሆናቸው ታውቋል፡፡

93.ስለ ሁኔታው የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ጥቅም ላይ የማይውሉ መለዋወጫዎችን በመመሪያው መሰረት ለማስወገድ ኮሚቴ በማቋቋም ሥራው የተጀመረ ሲሆን ሆኖም ግን በሂደት ላይ ሥራው መገኘቱን ገልፀዋል፡፡

94.በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካው ጥቅም ላይ የማይውሉ ብዛት ያላቸው ቋሚ ንብረቶች መገኘታቸው ለሌላ ተግባር የሚውልን መጋዘን ቦታ የሚይዙ፣በዓመታዊ ቆጠራ ወቅት የሰው ሃይልና ጊዜ የሚባክንባቸው ከመሆኑም በላይ በሌላ ድርጅት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ በሽያጭ ላይ ቢውሉ ለድርጅቱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

### የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ ግምገማን በተመለከተ

95.ማንኛውም ፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ተደርጎለት የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ ስለማስከተሉ ወይም አለማስከተሉ ተለይቶ እንዲታወቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

96.በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ የስኳር ፋብሪካው የአካባቢ ጥበቃ ክፍል በስኳር ኮርፖሬሽኑ በድርጅት ደረጃ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ምቹና የተዋበ የሥራ ቦታ መፍጠር የሚል ቢሆንም፤ በፋብሪካው የአገዳ አቅርቦት አካባቢ፣ በጥገና ጋራዥ፣ እንዲሁም በአካባቢው በሚገኙ መንገዶች በሚነሳ አቧራ ብናኝ ሰራተኛው በጤና መታወክ ላይ መሆኑን በአካል ለማየት ተችሏል፡፡

97. ስለ ሁኔታው ለደን ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሱፐር ቫይዘር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የሰራተኛውን ጤና ከመጠበቅ አንፃር የሰራተኛውን መኖሪያ ቤት አካባቢና መተላለፊያ መንገዶችን ገረጋንቲ የማልበስና ሞላስ የመርጨት ሥራ በመሥራት አቧራና ብናኝ የሚያመጣውን የጤና ችግር መከላከል ሥራ በሲቪል መስኖ መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ዘርፍ አስተዋፆ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

98. ኃላፊው ይህን ቢሉም የኦዲት ቡድኑ አካባቢዎቹን በአካል ተገኝቶ የተመለከተ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበለውም፡፡

99. የሥራ አካባቢን ከአካባቢ ተፅዕኖ ችግር በማስወገድ የሰራተኛውን ጤንነት በሚጎዱ/አስም እና የመተንፈሻ አካል/ ችግሮች ላይ የተፋጠነ መፍትሄ አለመስጠት የሰራተኛው ጤና በመታወኩ ምክንያት በሥራ ቦታው እንዳይገኝ ከማድረጉም በላይ ድርጅቱን ለሕክምና አገልግሎት ወጪ እንዲያወጣ ያደርገዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሀሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በስኳር ኮርፖሬሽን የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለተ በስኳር ኮርፖሬሽን እና በናሙና በኦዲቱ ተመርጦ በታየው በወንጂ/ሸዋ ማስፋፊያ ስኳር ፋብሪካ የታዩ ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሀሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

100. የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ የጨረታ እና ድርድር ሂደት በስኳር ኮርፖሬሽን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ/ሐምሌ 2003 ዓ.ም/ መሰረት በርካታ ተጫራቾችን ማግኘት እንዲቻል የስርጭት ሽፋን ባለው ጋዜጣ ላይ ማውጣትና ለኢምባሲዎችም የጨረታውን ጥሪ ማስተላለፍ እንደሚገባ በቁጥር 14.2.3.2 ላይ የተመለከተ ቢሆንም፤ ጋዜጣውና የድርድር ሁኔታውን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

101. ኮርፖሬሽኑ ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጂነሪንግ ፓኬጅ አቅርቦትን፣ ማንዋሎችን እና የመለዋወጫ እስፔስፊኬሽን ከተቋራጩ በውሉ መሰረት መረከብ አለመቻሉ የፋብሪካው ግንባታና ተከላ ሥራ በታቀደው ዲዛይን መሰረት መሰራቱን ለመገምገም የማያስችለው ሆኖ፤ ለወደፊቱም በፋብሪካው የሥራ ሂደት ዘመን ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስቸግር ሲሆን፤ የፋብሪካውን መላ አካላት የሙከራ ፍተሻ አስደርጎ አለመረከብም የተጓደሉ እና ለምርት ሂደቱ አስፈላጊ የሆኑ መለዋወጫዎችን በራስ አቅም ለመተካት አላስፈላጊ ወጪ እንዲወጣ የሚያደርገው መሆኑ፣

102. የስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ቅድመ- ጥናት ተደርጎላቸው አቅሙ ባላቸው ተቋራጮችና አማካሪዎች ካልተሰሩ፤ በታቀደ ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው በሀገሪቱ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንቅስቃሴ ፍጥነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ አገሪቷ ለሌላ ተግባር የምታውለውን በጀት ለሚታዘዙ ተጨማሪ ሥራዎች እንድታውል በማድረግ የሀገር ውስን ሀብትን ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይውል የሚያደርግ መሆኑ፣

103. ለሸንኮራ አገዳ መሬት መስኖ ልማት የሚጠኑ ጥናቶች እና የሚነደፉ ዲዛይኖች ጊዜ ተሰጥቷቸው ሊጠኑ እና ሊነደፉ የሚገባ ሆኖ፤ ተቋራጮችና አማካሪዎች በአሰሪው መ/ቤት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች በእቅድ በተያዘ ፕሮግራም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በታቀደ ጊዜ እና በተመደበ በጀት እንዲያጠናቅቁ ካልተደረገ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ አገሪቷ ለሌላ ተግባር የምታውለውን በጀት ለሚታዘዙ

ተጨማሪ ሥራዎች እንድታውል በማድረግ የሀገር ውስን ሀብትን ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይውል ማድረጉ፣

104.ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚሆኑ ማሳዎች በየዓመቱ በታቀደላቸው መሰረት ዝግጅት ተደርጎላቸው አለመተከላቸው ፋብሪካውን በአንድ ወቅት የግብዓት እጥረት እንዲያጋጥመው ከማድረጉም ባሻገር አድሜያቸው ያልደረሱ ማሳዎችን እንዲቆረጡ የሚደረስበት ሁኔታ ሊያደርስ ወይም ፋብሪካው እንዲቆም የሚገደድበት ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበት ደረጃ የሚያደርስ ሲሆን፤ ለተተከሉ የሸንኮራ አገዳ ማሳዎችም ቅድመ-ዝግጅት በማድረግ የተባይና የበሽታ መከላከል ሥራ አለመሥራት እንዲሁም የአገዳ ተክሉን በማፋፋት የሸንኮራ አገዳ ጁስ ይዘቱ/ሱክሮስ/ን የሚጠብቁ ዩሪያ ማዳበሪያና የፋብሪካ ተረፈ ምርት ማዳበሪያ በተፈለገው መጠን አለመስጠት ፋብሪካው ማምረት የሚችለውን የስኳር ምርት መጠን ማምረት የማያስችለው በመሆኑ በስኳር ምርት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ምንጭ በማሳጣት ለኪሳራ የሚዳርግ መሆኑ፣

105.ለእርሻ የሚሆኑ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎችን እና መለዋወጫዎቻቸውን በየእቅድ ዓመቱ በሚፈለገው መጠን አለማቅረብ ለስኳር ፋብሪካው ግብዓት ማቅረብ የማያስችል በመሆኑ በየዓመቱ ለማምረት የሚታቀደውን የስኳር ምርት መጠን ማምረት የማያስችል ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱ የህዝቦቿን ፍላጎት ለመደጎም ስኳር ከውጭ እንድታመጣ በማድረግ ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ መሆኑ፣

106.በስኳር ኮርፖሬሽን የግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ የክትትል እና ቁጥጥር መርሀ-ግብር በመዘርጋት የመለዋወጫ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ባለመደረጉ ምክንያት የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በየበጀት ዓመቱ የታቀደለትን የምርት መጠን እንዲያመርት አቅም ያልተገነባለት ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱ ልታገኝ የምትችለውን ገቢ እንድታጣ ምክንያት መሆኑ፣

107.በስኳር ኮርፖሬሽን ኮርፖሬት ፋይናንስ ከተሰጠው ተግባር በፋብሪካዎች እና በፕሮጀክቶች የሚካሄዱት ኢንቨስትመንቶች በታቀደላቸው ጊዜና ወጪ መካሄዳቸውን ማረጋገጥ የሚል ከመሆኑ አንፃር ኮርፖሬቱ ለፋብሪካው ወሳኝ ግብዓት የሆኑ እቃዎች ወደ መወረስ ደረጃ እስኪደርሱ ክፍያ አለመፈፀሙ ከፍተኛ ወጪ ተከፍሎባቸው ወደ ሀገር የገቡ እቃዎች በመወረስ ምክንያት ለታቀደላቸው ዓላማ እንዳይውሉ ከማድረጉም በላይ ለከፍተኛ የሀብት ኪሳራ የሚዳርግ ሲሆን፤

እንዲሁም በስኳር ኮርፖሬሽን ኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት ከተሰጠው ተግባር የፋብሪካዎች፣ የፕሮጀክትና የዋናውን መ/ቤት የግዥ ፍላጎት በመለየትና በጋራ በመግዛት ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ የሚል በመሆኑ ስኳር ፋብሪካው መለዋወጫ እጥረት በገጠመው ወቅት መፍትሄ ለማግኘት በማስረጃ ድጋፍ በጠየቀበት ጊዜ የኮርፖሬት ግዥ ክፍሉ የመፍትሄ አካል ባለመሆኑ ምክንያት ድርጅቱ በአፋጣኝ የአገዳ ጎታች ጋሪዎችን ባለማግኘቱ ለፋብሪካው የየቀን ተፈላጊ የአገዳ አቅርቦት ማቅረብ ባለመቻሉ በስኳር ምርት ላይ

አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲፈጠር ያደረገ ሲሆን፤ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ የተፈፀሙ ግዥዎችን ክትትልና ቁጥጥር

በማድረግ ለፈላጊው ክፍል በወቅቱ ሥራ ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ የሥራ ክፍሎች በበጀት ዓመት እቅድ የያዙትን መሥራት እንዳይችሉ በማድረጉ በፋብሪካው ምርት ሂደት ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑ፣

108.በስኳር ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ተግባር የተቀናጀ ውጤታማና ችግር ፈቺ ስርዓት በመዘርጋት ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ የንብረት አስተዳደር ማከናወን ቢሆንም ከዚህ አኳያ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ባለመሰራቱ በዓመታዊ ቆጠራ ወቅት ለሚታዩ ልዩነቶች ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

109.በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካው ጥቅም ላይ የማይውሉ ብዛት ያላቸው ቋሚ ንብረቶች መገኘታቸው ለሌላ ተግባር የሚውልን መጋዘን ቦታ የሚይዙ፣በዓመታዊ ቆጠራ ወቅት የሰው ሃይልና ጊዜ የሚባክንባቸው ከመሆኑም በላይ በሌላ ድርጅት ጥቅም ላይ የሚውሉ በሽያጭ ቢወገዱ ለድርጅቱ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑ፣

110.የሥራ አካባቢን ከአካባቢ ተፅዕኖ ችግር በማስወገድ የሰራተኛውን ጤንነት በሚጎዱ/አስም እና የመተንፈሻ አካል/ ችግሮች ላይ የተፋጠነ መፍትሄ አለመስጠት የሰራተኛው ጤና በመታወኩ ምክንያት በሥራ ቦታው እንዳይገኝ ከማድረጉም በላይ ድርጅቱን ለሕክምና አገልግሎት ወጪ እንዲያወጣ የሚያደርግ መሆኑ፣

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

111.ኮርፖሬሽኑ የስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ የጨረታ እና ድርድር ሂደት ባወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ሊያካሂድና ሂደቱን የሚያሳይ የተደራጀ ማስረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡

112.ኮርፖሬሽኑ  ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጂነሪንግ ፓኬጅ አቅርቦትን፣ ማንዋሎችን እና የመለዋወጫ እስፔስፊኬሽን የስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ ለማካሄድ በጨረታ ሂደት ከተመረጠ ተቋራጭ በውሉ መሰረት መረከብ እንዲሁም በማጠናቀቂያ ወቅት ፋብሪካው በተሟላ ሁኔታ ስለመሥራቱ የሙከራ ፍተሻ/ኮሚሽኒንግ/ በማድረግ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

113.ኮርፖሬሽኑ የስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ ፕሮጀክቶች ቅድመ- ጥናት ተደርጎላቸው አቅሙ ባላቸው ተቋራጮችና አማካሪዎች እንዲሰሩ በማድረግ በታቀደላቸው ጊዜና በተመደበላቸው ወጪ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

114.ለሸንኮራ አገዳ መሬት መስኖ ልማት የሚጠኑ ጥናቶች እና የሚነደፉ ዲዛይኖች ጊዜ ተሰጥቷቸው ሊጠኑ እና ሊነደፉ የሚገባ ሆኖ፣ ተቋራጮችና አማካሪዎች በአሰሪው መ/ቤት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች በእቅድ በተያዘ ፕሮግራም ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎ በታቀደ ጊዜ እና በተመደበ በጀት እንዲያጠናቅቁ ሊደረግ ይገባል፡፡

115.ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚሆኑ ማሳዎች በየዓመቱ በታቀደላቸው መሰረት ዝግጅት ተደርጎላቸው ሊተከሉ፣ ለተተከሉ የሸንኮራ አገዳ ማሳዎችም ቅድመ-ዝግጅት በማድረግ የተባይና የበሽታ መከላከል ሥራ ሊሰራ እንዲሁም የአገዳ ተክሉን በማፋፋት የሸንኮራ አገዳ ጁስ ይዘቱ/ሱክሮስ/ን የሚጠብቁ ዩሪያ ማዳበሪያና የፋብሪካ ተረፈ ምርት ማዳበሪያ በተፈለገው መጠን በመስጠት ለፋብሪካ ግብዓት የስኩሮዝ ይዘቱ 13.48%  የሆነ የሸንኮራ አገዳ ምርት ሊመረት ይገባል፡፡

116.ኮርፖሬሽኑ ለእርሻ የሚሆኑ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎችን እና መለዋወጫዎቻቸውን በየእቅድ ዓመቱ በሚፈለገው መጠን ሊያቀርብ ይገባል፡፡

117.በስኳር ኮርፖሬሽን የግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ  የክትትል እና ቁጥጥር መርሀ-ግብር በመዘርጋት የመለዋወጫ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ በማድረግ  የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በየበጀት ዓመቱ የታቀደለትን የምርት መጠን እንዲያመርት እንዲያሟላ ሊያደርግ ይገባል፡፡

118.ኮርፖሬሽኑ ሀገር ውሰጥ ወደብ የደረሱ እቃዎች ከመወረሳቸው በፊት አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም ለታቀደላቸው ዓላማ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

119. ኮርፖሬሽኑ  በዓመታዊ ቆጠራ ወቅት ለሚታዩ ልዩነቶች ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

120.ኮርፖሬሽኑጥቅም ላይ የማይውሉ  ቋሚ ንብረቶችን ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ሊያስወግድ ይገባል፡፡

121.ኮርፖሬሽኑ የሥራ አካባቢ ለሰራተኛው ጤንነት ምቹ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡